ለተኣምረ ማርያም አትከራከር

ቴዎድሮስ ደመላሽ

© ቴዎድሮስ ደመላሽ
የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።።
All right reserved

2003 ዓመተ ምሕረት.

<u>የአዘጋጁ አድራሻ</u>
ስልክ +251 94 66 57 513
የመልእክት ሳጥን ቁጥር 29783 ዐዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
E-mail: tewoderosdemelash@gmail.com
Facebook: www.facebook.com/tewoderodemelash

ምስጋና

- በምሕረቱ እስከዚህ ላቆየኝ አምላኬና አባቴ፣
- በዚህ መልኩ እውነትን እንድገልጽ ምክንያት ለሆኑኝ፣
- ጽሑፉን ከማንበብና ከማረም ጀምሮ ለጎትመት እስኪበቃ ድረስ አብሮኝ ለደከመው ወንድም፣
- መጽሐፉን ለማሳተም በገንዘብ የደገፉኝን ወገኖቸና
- ዘወትር ስለእኔ ለሚጸልዩት ለባለቤቴና ለእናቴ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።።

ማውጫ

መግቢያ 4
'ክብር ለሚገባው ክብርን መስጠት' እንዴት? 6
ይበል ያሰኛል 7
የተለየ ክብር 8
የመዳናችን ምክንያት 10
ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ 10
"ቅዱሳንን አናመልክም" 12
ሁለቱ ማርያሞች 16
"የትኛው መጽሐፍ?" 17
ተኣምረ ማርያም ለምን ተጻፈ? 21
"ጳውሎስ እንዳለ" 23
"ይገለጣ መጽሐፍ ቅዱስ" 26
ፍጥረት ሁሉ ማርያምን ለማመስገን ተፈጠሩ 29
ያዳነን የማርያም ሥጋ ነው 31
ባለውለታችን ማን ነው? 34
ሐዋርያት ስለማርያም መስበካቸው 36
ማርያም የጸጋ መድኀኒት ናት 41
የቤት ሥራ ለመምህር ታሪኩ 45
ማጠቃለያ 47
ዋቢ መጻሕፍት 50

መግቢያ

ክርስትና መርጠው የሚኖሩት ሕይወት ነው፤ ክርስቲያን ለመሆን የሚፈልግ ማንም ሰው ያለማንም ገፋፊ በገዛ ምርጫው ነው ክርስቲያን መሆን የሚኖርበት፡፡ እንዲህ ሲሆን ደግሞ መርጦ ስለተከተለው የሕይወት መንገድ ለሰው ሁሉ እንዲናገር የጌታው ፍቅርና እርሱ የሞተላቸው ሰዎች መዳን ጉዳይ ግድ ይለዋል፡፡ ስላዳነው ጌታ የሚመሰክረው በሙሉ እምነት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል በሚያዘው መሠረት ሊሆን ይገባል፡፡ በቃሉ ላይ አንዳች ቢጨምር ወይም ከቃሉ ላይ አንዳች ቢቀንስ ከእግዚአብሔር ያልሆነን መልእክት እያስተላለፈ ነው፡፡ ይህን በማድረጉ ብዙዎችን ወደጥፋት ለመንዳት ምክንያት ይሆናል፡፡ በዚህ ዘመን በአንዳንዶች ዘንድ እየሆነ ያለውም ይኸው ነው ማለት ይቻላል፡፡

ይህ መልእክት እንዲዘጋጅ ያስፈለገበት ምክንያት፣ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ሊላት የሚገባትን የኢየሱስን እናት ማርያምን ከፍና ዝቅ ለማድረግ አይደለም፤ ወይም ለኢትዮጵያ ክርስትና ታላቅ ሥራ የሠራችውንና አሁን ላይ ያለን እኛ በነጻነት ክርስትንና በእናት ምድራችን ላይ እንድንከተልና እንድንመሰክርም መጽሐፍ ቅዱስን፣ ክርስትናንና ሌሎች ጠቃሚ ነገሮችን እኛ ዘንድ ያደረሰችውን ቤተ ክርስቲያን አለአግባብ መናገርም አይደለም፡፡ ነገር ግን እኛ ክርስቲያኖች ነን፤ ክርስቲያን እንድንባል ደግሞ ዋጋ የከፈለልን ክርስቶስ ብቻ ነው፤ አሁን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው መጽሐፍ ክርስቶስ ካስተማረው የተለየ እንግዳ ትምህርትን እያስተማረ ነውና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሊመሳከርና በመጽሐፍ ቅዱስ ሊዳኝ ይገባል ለማለት ብቻ ነው፡፡

ይህን መልእክት ተንተርሶ በጭፍን ተሰደብን፤ ተደፈርን የሚል ሰው ካለ ግን፣ ወተቱን ማጥቆር ማሩን ማምረር ልማዱ የሆነን ሰው ይመስላል፤ ስለዚህ አንባቢው ከዚህ ዓይነቱ ሰው እንዲርቅና በራሱ አንብቦ እውነታውን እንዲያገናዝብ ይጠየቃል። ክርስትና እኔ ዐውቅልሃለሁ፤ እኔ እጾምልሃለሁ፤ አንተ ዝም ብለህ ሥራህን ሥራ፤ የሚባል ሃይማኖት አይደለም። አንባቢ ሆይ! ሁሉም በየራሱ ሥራ ነውና የሚጠየቀው በራስዎ አንብበው በራስዎ እንዲወስኑ እግዚአብሔር ይርዳዎ።

‘ክብር ለሚገባው ክብርን መስጠት’ እንዴት?

ክብር ለሚገባው ክብርን መስጠት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ ይህን ሳያደርግ ግን ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው ቢኖር ራሱን እያታለለ ያለ ሰው መሆኑን ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ክብር እየሰጠሁ ነው በሚል ሽፋን አምልኮ ባዕድ መፈጸም እጅግ ትልቁ ኀጢአት ነው፡፡ በዚህ ዘመን ብዙዎች የእግዚአብሔርን ቃል የታዘዙ እየመሰላቸው፥ "እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ" የሚለውን ቃል ዘንግተው በአምልኮ ባዕድ ውስጥ ተዘፍቀዋል፡፡ ንስሓ በመግባት ፈንታም ለኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥራቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ ፍለጋ ዕድሜያቸውን እየጨረሱ ነው፡፡

በቅርቡ "ቴቄል" በሚል ርእስ በተኣምረ ማርያም ውስጥ የተጻፉትን ኢመጽሐፍ ቅዱሳውያን ትምህርቶችንና የተሳሳተ መልእክት ያላቸውን ጽሑፎች ለይተው በማውጣት ዘማሪ ኤፍሬም ከተማ በቪሲዲ ላቀረቡት መልእክት፥ መምህር ታሪኩ አበራ "ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ" በማለት ምላሽ ለመስጠት ሞክረዋል፡፡

ዘማሪ ኤፍሬም ከርእሳቸው ጀምረው "ቴቄል" ያሉ ሲሆን፣ መምህር ታሪኩም እንዲሁ በመልእክታቸው መጨረሻ ላይ "ቴቄል" (ነ፡17፡36 ደቂቃ) የሚለውን ቃል ተጠቅመው ሐሳባቸውን ይደመድማሉ፡፡ ለማንኛቸው መልእክት ነው "ቴቄል" የሚለው ቃል ተገቢ የሚሆነው? የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ለዚህ እንዲረዳው የሁለቱንም መልእክት በማስተዋል ከተከታተለ በኋላ ሁለቱም በተኣምረ ማርያም ዙሪያ ያነሧቸውንና ከመጽሐፍ ቅዱስ የጠቀሷቸውን ክፍሎች ለመመልከት ሞክሮ በመጨረሻ ላይ እውነትም "ቴቄል" ብሏል፡፡

መምህር ታሪኩ የሚያምኑት ነገር ስለተነካባቸው ምላሽ ለመስጠት መነሣታቸው ትክክል ነው፡፡ ምላሽ ለመስጠት የሄዱበትም መንገድ ሰላማዊ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ጉዳዩን በሁለት አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተደረገ ምልልስ ለማስመሰል ያደረጉት ነገር ብዙዎችን አሳዝኗል፡፡ የብዙዎችን ልብ የነካውና ለምን እንዲህ ማድረግ አስፈለገ? እንዲሉ ያደረገው መምህሩ በየመንገዱ እንዲለጠፍ ባደረጉት ማስታወቂያቸው ላይ "መሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ለሰነዘረችው ጸያፍ ስድብ የተሰጠ ምላሽ" ሲሉ ያሰፈሩት ገበያ ጠሪ ማስታወቂያ ነው፡፡

አንዳንድ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የስብከታቸው ማጣፈጫ ጨው ወይም የስብከታቸው ማጠንጠኛ አንኳር ነጥብ ያደረጉት "መናፍቃን" የሚለውን ክፉ ስም ነው፡፡ እነዚህ አገልጋዮች ይህን ስላሉ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተሳደቦች ቢባል ትክክል ይሆናልን? ለምሳሌ፡- የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አማኝ ሆነው የእግዚአብሔር ፍጡር የሆኑትን ሰዎች "አውሬ" አስመስለው ያቀረቡትን መምህር ስብከት መነሻ በማድረግ፥ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተሳደቦች የሚል ሰው ቢኖር ትክክል ሊሆን ነው ማለት ነውን?

ይበል ያሰኛል

መምህር ታሪኩ መልስ ለመስጠት የሞከሩበት አቀራረብ መልካም ነው፡፡ እርሳቸው እንዳሉት ሰው የሚያምነውን ነውና ለማስተላለፍ የሚሞክረው እርሳቸው እምነታቸውን እንዲህ በጨዋነት ለማስተላለፍ መሞከራቸው ደስ የሚያሰኝ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ በመልእክታቸው ውስጥ ለዘማሪ ኤፍሬም መልእክት ለማስተላለፍ

ሲፈልጉ "ወንድሜ" የሚለውን ቃል መጠቀማቸው በተሻለ ሁኔታ ያላቸውን ጨዋነት ያሳያል፡፡ ይህ መልካም መንፈስን የተላበሰ የመልስ አሰጣጥ ባህላችን ቢዳብር፣ ሩቅ ለሩቅ ሆነን የምንወራወራቸው የቃላት ድንጋዮች ቀርተው ወደሰላማዊ ውይይት እንጠጋለን የሚል ተስፋን ያሳድራል፡፡

ሌላው የመምህሩ መልእክት መልካም ገጽታ፣ ከዚህ በፊት ለወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ከኦርቶዶክስ አገልጋዮች ምላሽ ሲሰጥ የማይጠፉ የነበሩትን ዘለፋና መልካም መንፈስ የሌላቸውን ቃላቶች አለመጠቀማቸው ነው፡፡ ይህም በተሻለ ሁኔታ መቀራረብንና ወንድማማችነትን የሚያጠነክር መልካም ጎዳና ነው፡፡

"የተለየ ክብር"

መምህሩ ለምን "ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ" በሚለው ርእስ መማማር እንዳስፈለገ ሲገለጹ፡-

> "በዚህ ርእስ የምንማማረው አንድ መሠረታዊ ነገር ለማስጨበጥ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የተለየ ቦታ፣ የተለየ ምስጋና፣ የተለየ ክብር በካህናትና በምእመናን ዘንድ ይሰጣታል" (4፡17-4፡45 ደቂቃ) ብለዋል፡፡

እዚህ ላይ የተለየ ክብርና ምስጋና ያሉት ነገር ግልጽ አይደለም፡፡ እንደዚህ ግልጽነት የጎደላቸው አስተምህሮቶች ናቸው ብዙዎችን ወደተሳሳተ ሕይወትና ወደጥፋት እየወሰዱ ያሉት፡፡ ለሕዝብ ቃለ እግዚአብሔርን ለማስተማር መድረክ ላይ የሚወጡ መምህራን ሁሉ

የሚያስተምሩት ትምህርት ግልጽነት ያለውና የማያሻማ ቢሆን ለፍሬ ከመብቃቱም በላይ ለብዙዎች በረከት ይሆናል።

ይህ የመምህሩ ትምህርት ግልጽነት ይጎድለዋል የተባለው፣ ለማርያም ለምን ይህ ልዩ ምስጋና፣ ልዩ ክብርና የተለየ ቦታ አስፈለጋት? የሚለውን መልስ ሳይመልስ በማለፉ ነው። መምህሩ ራሳቸው ሲናገሩ የሆነ ነገር ላደረገልን ሰው ምስጋና እናቀርባለን ብለዋል። እርግጥ "ሰማያዊውን አምላክ በማሕፀኗ ያስተናገደች፣ ለዓለም ሁሉ የመዳን ምክንያት አድርጎ ጌታ የመረጣት ቅድስት እናት ስለሆነች" (4፡47-57 ደቂቃ) የሚል ምክንያት አቅርበዋል። ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ድንግል ማርያም የጌታ እናት መሆኗን አይክድም፤ በጌታ እናትነቷ የሚገባትን ክብር የሚነፍግ ክርስቲያንም ሊኖር አይችልም። ነገር ግን ለዚህ ክብር የመረጣት ራሱ እግዚአብሔር እንጂ ማርያም በራሷ የሆነችው አይደለምና <u>የራሷ የሆነ</u> ምን ነገር ኖሮ ይሆን ልዩ የሆነ ምስጋና ይገባታል ያሉት? በዚህ መነሻነትስ ነገሩን ለጥጦ ያልተጻፈላትንና ያልተነገረላትን 'እርሷ የመዳን ምክንያት ናት' ማለት ፍጹም ኑፋቄ አይደለምን?

ሌላው ግልጽነት የጎደለው መልእክት ደግሞ ከማን የተለየ ምስጋና እንደሚገባት አለመገለጹ ነው። ምናልባት ከእግዚአብሔር የተለየ ምስጋና ለማለት ተፈልጎ ይሆን? ይህ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ምስጋናና ክብር ለፍጡር በመስጠት እግዚአብሔርን መበደል የተሳሳተ ትምህርት ነው። እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ ያለው ጌታ፣ እንደዚህ በሚያደርጉ ሁሉ ላይ ቀጣው ጽኑዕ ነው። ስለዚህ በራሳችንና በትውልድ ላይ መርገምን ባናስቀምጥ መልካም ነው።

የመዳናችን ምክንያት

መምህር ታሪኩ ለዓለሙ ሁሉ መዳን ምክንያት የሆነችው ድንግል ማርያም እንደሆነች በተደጋጋሚ አስተምረዋል (4፡51፤ 41፡35-42፡30፤ 44፡40-45፡00 45፡38-46፡15 ደቂቃ ላይ ይመልከቱ)። በዚህ ንግግራቸው ለዓለሙ ሁሉ መዳን ማርያም ያለምንም ድርድር የመጀመሪያ አስፈላጊ አካል እንደሆነች አድርገው ነው ያቀረቡት፤ ይህ ግን ትልቅ የስሕተት ትምህርት ነው።

ለሰው ልጆች ሁሉ መዳን የመጀመሪያውም ሆነ የመጨረሻው አስፈላጊ አካል እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ብቻውን ከሁሉ በላይና ለሁሉ በቂ ነው። የእርሱ ረዳት አድርገን የምናስቀምጣቸው ሁሉ ያንን ለማድረግ ብቃቱም ሆነ ችሎታው የሌላቸው ናቸው።

መምህሩ መጽሐፍ ቅዱስ ለመዳናችን ምክንያት የሆነው ክርስቶስ እንደሆነ "ለሚታዘዙለት የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው" (ዕብ. 5÷10) በማለት የገለጸውን አላነበቡ ይሆን? 'ማርያም ምክንያተ ድኂን ናት' እያሉ የሚያስተምሩት ይህን ቃል አንብበውትና እያወቁት ከሆነ ግን ሕዝብን እያሳቱ ነውና እባክዎ ወደቃለ እግዚአብሔር ይመለሱ።

ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

መምህር ታሪኩ "ቴቄል" ስለተባለው ስብከት ሲናገሩ፡-

> "የእመቤታችንን ክብር የሚነቅፍ የእመቤታችንን ታላቅነት የሚያንጓጥጥ በተለይም ለዘመናት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አከብራ የያዘችውን ተኣምረ ማርያምን የሚያንቋሽሽ ስብከት"

አድርገው ነው ያቀረቡት (5፡20-5፡48 ደቂቃ)።

መምህሩ እንዴት እንደተመለከቱት ግልጽ ባይሆንም የኢየሱስ እናትና መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክርላት ማርያም እና በተኣምረ ማርያም ላይ በማርያም ስም እንድትጠራ የተደረገችው ሴት የስም እንጂ ሌላ ምንም ዝምድና የላቸውም፡፡ ይህን ግን መምህር ታሪኩ ያስተዋሉት ኣይመስልምና "ድንግል ማርያም ጨካኝ ነፍሰ ገዳይ ደም አፍሳሽና የበረሃ እርኩስ መንፈስ ያደረባት ሴት ነች" የሚል ነገር ዘማሪ ኤፍሬም እንደተናገሩ በማስመሰል በሲዲያቸው ጀርባ ላይ ጽፈዋል፡፡ ዘማሪው ለመናገር የፈለጉት ግን፡-

በተኣምረ ማርያም ላይ በማርያም ስም የምትጠራዋ ሴት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመልካም ስብእና ከምትታወቀዋ ማርያም ጋር ምንም ዓይነት ተዛምዶ የላትም፡፡ የተኣምረ ማርያሟ ማርያም ሰው እንዲሞት አድርጋለች፤ ለራሷ ክብር ቅድሚያ ትሰጣለች፤ ክብሯን በተመለከተ ማንም ከእርስዋ ጋር ሊደራደር እስከማይችል ድረስ ራሷን ከፍ ከፍ አድርጋለች፤ "የመጽሐፍ ቅዱሷና እውነተኛዋ የጌታችን እናቱ የሆነችው ቅድስት ድንግል ማርያም ደግሞ እንደዚህ ዓይነት ባሕርይ የላትም፡፡ እንደውም የጌታችን የመድኀኒታችን እናት የሆነችው እውነተኛዋን ማርያምን ስም ለማጉደፍ በኣጋንንት የተሸረበ ሤራ ነው" የሚል ነው ("ቴቄል" 33፡26-33፡49 ደቂቃ)፡፡

አሁንም መምህሩ ግልጽ እንዲሆንላቸው የሚገባው ነገር በተኣምረ ማርያም ውስጥ የቀረበችውና በማርያም ስም የምትጠራው ሴት ከኢየሱስ እናት ማርያም ጋር ምንም ተዛምዶ የሌላት መሆኑን ነው፡፡ ስንት ማርያም ነው ያለው ብለው ኣድማጮቻቸውን ጠይቀው አንድ ማርያም ብቻ እንዳለች በማስመሰል ካቀረቡ በኋላ፣ ሁለቱን የተለያዩ

እንደሆኑ አድርጎ ማቅረብ የጌታን እናት መንቀፍ እንደሆነ አድርገው ተናገረዋል (9፡25-10፡25 ደቂቃ)።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በሚቃረነው ትምህርቱ ተኣምረ ማርያምን ቢነቀፍ ተገቢ ነው። በዚህ መንገድ መንቀፉ ማርያምን መንቀፍ መስሎ የሚታያቸው ሰዎች ካሉ ግን ተሳስተዋል። በማርያም ስም የተሳሳተ ትምህርት ወደቅድስት ቤተ ክርስቲያን አሾልከው ለማስገባት የፈለጉ ሰዎች ያስቀመጡትን የስሕተት ትምህርት መቃወም ማርያምን መቃወም አይደለምና አንባቢው ይህን ቢረዳው መልካም ነው።

ቅዱሳንን አናመልክም

ሊመለክና ሊወደስ የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ይቀበላል። አሁን ያለውን እውነታ ስንመለከት ግን ንግግርና ተግባር ለየቅል እየሆኑ ነው። መምህር ታሪኩ አጠንክረው በቤተ ክርስቲያናችን ከእግዚአብሔር ሌላ የሚመለክ የለም የሚል መልእክታቸውን ያስተላለፉት እንዲህ በማለት ነው፡-

> "ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ክብርና ለቅዱሳን የምንሰጠው ክብር ደግሞ ለየቅል ነው። እግዚአብሔርን የአምልኮ ክብር፣ የአምልኮ ስግደት፣ የአምልኮ ምስጋና እናቀርብለታለን። ለቅዱሳን ደግሞ አምልኮ አይደለም የምንፈጽምላቸው እመቤታችንን የሚያመልካት አለ እንዴ? ድንግል ማርያም ፈጠረችኝ፣ ድንግል ማርያም ተሰቀለችልኝ የሚል ኦርቶዶክሳዊ አለ እንዴ? የለም! ፈጽሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድም ቦታ የጻፈችው የሰበከችው ትምህርት የለም። ... ክብር ለሚገባው ክብር መስጠት

ይገባል ወይስ አይገባም? ግን ክብር የሚሰጠው እንዴት ነው? አሁን ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በሥራ እንተርጉመው ካልን እንዴት ነው የምንተረጉመው? ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ አለ፡፡ ለእግዚአብሔር ክብርን እንሰጣለን፤ በምን? በአምልኮ በምስጋና፡፡ ለቅዱሳን ክብርን እንሰጣለን፤ በምን? በምስጋና፣ ግን አናመልካቸውም፡፡ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ ስለሚል መጽሐፍ እናከብራለን" (7፡11-7፡54፤ 31፡23-31፡55 ደቂቃ)፡፡

መምህር ታሪኩ ሊመለክ የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ ላይ ተቃውሞ ያላቸው አይመስልም፡፡ በስብከታቸው "እርግጥ ነው ፍጥረታት በሙሉ እግዚአብሔርን ማመስገን አለበት ... ከምንም በላይ፣ ከማንም በፊት ምስጋና የሚገባው የነገሥታት ንጉሥ እግዚአብሔር ነው" ሲሉ አስተምረዋል (31፡56-32፡53 ደቂቃ)፡፡ ብቻውን ሊመለክ የሚገባውን አምላክ እንዴት አድርገን ነው አምልኮአችንን የምናቀርብለት በሚለው ላይ ግን ምንም ማለት አልፈለጉም፡፡

ከዚህም ሌላ የእግዚአብሔር ክብርና የቅዱሳን ክብር ለየቅል ነው ብለዋል፤ ልዩነቱ በምን ላይ እንደሆነ ግን ያቀረቡት አንዳች ነገር የለም፡፡ ይህም አድማጮቻቸውን ግራ ከማጋባቱም በላይ፣ የሚያስተላልፉትን መልእክት ሰምተው ብዙዎች ወደስሕተት ትምህርት ሊሄዱ እንደሚችሉ አለመረዳታቸውን ያሳያል፡፡

ሌላው መምህር ታሪኩ ለቅዱሳን የሚቀርብላቸው አምልኮ አይደለም ያሉትና እመቤታችንን የሚያመልካት አለ እንዴ? ሲሉ ያቀረቡት ሐሳብ በቃላት ደረጃ ሲታይ ትክክል ቢመስልም፣ በተግባር የሚታየው ግን ተገላቢጦሹ ነው፤ ለምሳሌ፡- ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ

እንደደረሰው በሚነገረው በመስተብቊዕ ዘማርያምና በመስተብቊዕ ዘመስቀል ላይ "ኑ ለንግሢ እንስገድ እናመስግናትም /እንገዛላትም ... ለሷ ክብርና ስብሐት ይገባታል፤ ከልጇም ጋራ አምልኮና ስግደት ... ለነዚህ ሁለቱ ፍጡሮች የፈጣሪ ስብሐት ይገባቸዋል በክብራቸው ተካክለዋልና" በማለት ለአምላክ ብቻ የሚገባው አምልኮና ስግደት ለፍጡራን ሲሰጥ ይታያል ("ደቂቀ እስጢፋኖስ በሕግ አምላክ" ትርጉም በጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር) ገጽ 36-41)። ይህም ዘወትር በቤተ ክርስቲያን በማኅበር የሚጸለይ ጸሎት ነው፤ ታዲያ ይህ አክብሮት ነው አምልኮት?

ከዚህ ሌላ መምህሩ ማርያም ፈጠረችኝ፣ ድንግል ማርያም ተሰቀለችልኝ የሚል ኦርቶዶክሳዊ አለ እንዴ? በማለት ስላቀረቡት ጥያቄና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአንድም ቦታ እንዲህ ብላ የጻፈችው ነገር እንደሌለ በማስመሰል ስላነሡት ነጥብ ጥቂት ማለት ያስፈልጋል። ይህን የመምህሩን መልእክት የሰማ ሰው እርሳቸው ቤተ ክርስቲያናቸውን አያውቋትም፤ ወይም ለመኖር ብለው ነው፤ አሊያም ሆነ ብለው ሰውን ለማሳሳት ጥረት እያደረጉ ነው ብሎ ቢያስብ ስሕተት አይሆንበትም።

መምህሩ ማርያም ፈጣሪ እንደሆነች የሚናገር አንድም መጽሐፍ እንደሌለ እርግጠኛ ሆነው ይናገሩ እንጂ፣ በኪዳነ ምሕረት ዚቅ ላይ "ብቻዋን ታላላቅ ብርሃናትን ለፈጠረች ለመድኀኒታችን ለድንግል ማርያም ኑ እንስገድላት ለእርሷም እንገዛ" የሚል ንባብ አለ ("የዘመናት እንቆቅልሽ ሲፈታ" በመሪጌታ ሠረቀ ብርሃን ዘወንጌል ገጽ 50)። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻውን ታላላቅ ብርሃናትን የሠራው እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን እየተናገረ፣ ይህን የፈጣሪነት ግብር ለማርያም የሰጠውን ይህን መጽሐፍና

መሰሎቹን አዋልድ መጻሕፍት በዚህ ትምህርታቸው ተሳስተዋል ለማለት የመምህር ታሪኩ አንደበት ለምን ተዘጋ?

ማርያም ብቻ አይደለችም መርቆርዮስም ፈጣሪ እንደሆነ እንዲህ ተጽፏል፡- "አቤቱ ሰማይን በከዋክብት የሸፈንክ፣ ምድርንም በዕፀዋት (በአበቦች) ያስጌጥክ መርቆሬዎስ ሆይ! ለስምህ እገዛለሁ፤ ስለጎያልነትህም አመሰግናለሁ፤ ወደአንተ የሚመጣውን የሥጋ ለባሽ ሁሉ ጸሎት ስማ፤ ይቅርታህንም አታዘግይብን፡፡ ብርሃንህና እውነትህን ላክ፤ እነርሱ ይምሩኝ ወደ ቅድስናህ ተራራና ወደማደሪያህ ይወሰዱኝ" ("የዘመናት እንቆቅልሽ ሲፈታ" በመሪጌታ ሰረቀ ብርሃን ዘወንጌል ገጽ 33፡፡ "ገድል ወይስ ገደል?" በመምህር ጌታቸው ገጽ 24)፡፡

ዲያቆን አግዛቸው ተፈራ መጽሐፈ ዚቅ በተሰኘው የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ላይ ያገኙትን እንደጠቀሱት መርቆሬዎስ የዓለም ፈጣሪ ብቻ አይደለም የተባለው፤ ስለ ዓለሙ ሁሉ ጎጢአት ሲል መከራን ተቀብሎ ተሰቀሏልም ተብሏል፡፡ "የመርቆሬዎስን ቸርነት ትሕትናና የዋህነት እንናገራለን፡፡ ስለሰው ፍቅር መከራን የታገሠ÷ ሰማይን እንደ መጋረጃ የሰቀለው በዕንጨት ላይ ተሰቀለ፤ ሰማይን በከዋክብት የሸፈነ የሾህ አክሊልን ተቀዳጀ" ("የተቀበረ መከሊት" ገጽ 89-90፡፡ "የዘመናት እንቆቅልሽ ሲፈታ" መሪጌታ ሰረቀ ብርሃን ዘወንጌል ገጽ 29)፡፡

እነዚህን የዚቅ ጥቅሶች ከመምህሩ መልእክት ጋር እንዴት ማስታረቅ ይቻላል? መምህር ታሪኩ ማርያም ፈጣሪ ነች የሚል መጽሐፍ ፈጽሞ የለም ቢሉም፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፍ (መጽሐፈ ዚቅ) ግን ማርያም ፈጣሪ እንደሆነች ይናገራል፤ ታዲያ ማን ይሆን የተሳሳተው? መምህሩ ወይስ መጽሐፉ?

ሁለቱ ማርያሞች

መምህር ታሪኩ በተኣምረ ማርያም ውስጥ ያለችውና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸችው ማርያም አንድ መሆናቸውን እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፤

> "የክርስቶስ እናት ስንት ነች? አንዲት ነች በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስምንት ማርያሞች አሉ፡፡ ... የጌታ እናት ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ያለችው በተኣምረ ማርያም ውስጥም የተገለጸችው ግን አንዲቷ የሐናና የኢያቄም ፍሬ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ነች፡፡ ፕሮቴስታንቱ ሰባኪ ግን የተኣምረ ማርያሟ ማርያም ጨካኟ፣ አረመኔ፣ መናፍስት ጠሪ፣ ክፉ፣ ደም አፍሳሽ የሆነች ሴት ነች፡፡ የመጽሐፍ ቅዱሷ ማርያም ግን ከዚህ የተለየች ነች እያለ እመቤታችንን ለመንቀፍ አንደበቱን ሲከፍት ሰምተናል" (9፡25-10፡25 ደቂቃ) ብለዋል፡፡

እርግጥ ነው የጌታ እናት አንዲት ናት፤ ተኣምረ ማርያም በስሟ የተደረሰላት ማርያምም እርሷ መሆኗን መካድ አይቻልም፡፡ ነገር ግን በስሟ የተደረሰው ብዙው ነገር ከእርሷ ማንነትና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተገለጸው የእርሷ ባሕርይ ጋር ፈጽሞ አይመሳሰልምና ተኣምረ ማርያም በስሟ ተደረሰ እንጂ እርሷን አይወክልም መባሉ ትክክል እንጂ ስሕተት አይሆንም፡፡ እንዲህ መባሉ ታዲያ መምህሩን ለምን ቅር አሰኛቸው? ‘ጅብን ሲወጉ በአህያ ይጠጉ’ እንደሚባለው፣ ማርያምን ለሙግታቸው ሽፋን አደረጓት እንጂ እየተሟገቱ ያለው ስለ ማርያም ሳይሆን ስለ ተኣምረ ማርያም መሆኑ ከአቀራረባቸው ግልጽ ሆኗል፡፡ ነፍስ ያጠፋችውንና እግዚአብሔርን ለማታለል ሞክራለች የተባለችውን

የተኣምረ ማርያሚን ገጸ ባሕርይ የጌታን እናት ማርያምን አትወክልም፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊም አይደለም ማለት የኢየሱስን እናት መንቀፍ እንዴት ሊሆን ይችላል? አላስተዋሉም እንጂ የተኣምረ ማርያሚ ገጸ ባሕርይ የጌታ እናት ናት ማለት፣ የኢየሱስን እናት መንቀፍና መልካም ስሟን ማጉደፍ ነው፡፡ ስለዚህ ቀድመው በሩን ይዘው እኔ ነኝ ትክክል ማለት እውነተኛ አያደርግዎትም፡፡

ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተጻፈው መልካምና ግሩም አብነት ያላት ሴት ናት፡፡ ይህን አስተባብሎና ክዶ፣ ቅድስት ማርያም የሌላትን መጥፎ ባሕርይ ሥሎ በቅድስት ማርያም ላይ አንደበቱን የሚያላቅቅ ሰው ቢኖር ግን እርሱ ከእግዚአብሔር አይደለም፡፡

"የትኛው መጽሐፍ?"

አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወት ያድግ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ አለበት፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ መልእክት ያላቸውን ጽሑፎች ሊያነብ ይችላል፡፡ እነዚህ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው የተጻፉ መጻሕፍት ግን መጽሐፍ ቅዱስን ሊተኩም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሊነጻጸሩ አይችሉም፡፡

መምህር ታሪኩ ተአምራትን፣ ገድላትንና ድርሳናትን እንዲሁም ሌሎች የጸሎት መጻሕፍትን በእግዚአብሔር መንፈስ እንደተጻፉ አድርገው አቅርበዋል፡፡

"ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፡- በ2ኛ ጢሞ. 3÷15 ላይ ‘የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ’ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አላለም፤ ‘የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ

ለትምህርት፣ ለተግሣጽ፣ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ደግሞ ለምክር ይጠቅማል' ይላል። የትኛው መጽሐፍ? መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ? ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ብቻ ነው? አይደለም፤ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ መጻሕፍት ሁሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ድርሳናት የተጻፉት በእግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ በዲያብሎስ መንፈስ አይደለም። ተኣምረ ማርያም የተጻፈው በእግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ቅዱስ ደቅስዮስ ይህን የተኣምር መጽሐፍ የጻፈው መንፈስ ቅዱስ በገለጸለት መጠን ነው። በሉሲፈር አጋዥነት አይደለም። የቅዱሳን አባቶች የገድል መጻሕፍት የተጻፉት በእግዚአብሔር ኃይል ረዳትነት ነው። እነዚህ መጻሕፍት ናቸው ቅዱስ ጳውሎስ ለትምህርት ለተግሣጽ ለምክር ይጠቅማሉ ያለው" (13፡58-15፡20 ደቂቃ)።

ተኣምረ ማርያም ግን የጻፈኝ ደቅስዮስ ብቻ ነው አላለም፤ በእነ አባ አብርሃም አባ ማርቆስና አባ ማቴዎስም ጭምር ተጻፍሁኝ ይላል ("ተኣምረ ማርያም" መቅድም ቁ. 1-7 ገጽ 8) በተለይ የደቅስዮስን ሥራ የሚገልጸው እንዲህ በማለት ነው።

"ስሙ ደቅስዮስ የሚባል ኤጴስ ቆጶስ ጥልጥልያ በምትባል አገር በተሠራች ቤተ ክርስቲያን እንደነበረ ተናግረዋል። ይኸውም የተባረከ ሰው ነበረ። አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ክብርት እመቤታችንን በፍጹም ልቡናው የሚወድ፣ በተቻለው ሁሉ የሚያገለግላት፣ ከፍቅሩም ጽናት የተነሣ አስቦ ተኣምሯን የሚናገር መጽሐፍ <u>ሰበሰበ</u>። የምእመናንን ክብር የምትሆን አምለክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች እመቤታችን ተገለጠችለት።

መጽሐፏን በእጅዋ ይዛ ወዳጇ ደቅስዮስ ሆይ! ባንተ ደስ አለኝ፤ ይህን መጽሐፍ ስለጻፍህልኝም አመሰገንሁህ። ከዚህም በኋላ ከእሱ ተሰወረች። ደቅስዮስም በራእይ ይህን ነገር ባየ ጊዜ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ክብርት እመቤታችንን ከመውደዱ የተነሣ ፈጽሞ ደስ አለው፤ እሷንም ስለወደደ ፍቅሯ እንደ እሳት አቃጠለው። ምን እንደሚያደርግም የሚሠራውን ያስብ ጀመር፤ የሷን ክብር እያበዛ ይጨምር ዘንድ።"

ከዚህ በኋላ ማንም ሰው አክብሮት የማያውቀውን ገብርኤል ማርያምን ያበሠረበት የተባለውን ቀን ለማክበር አስቦ አደረገው፤ ሌሎችም እርሱን ተከትለው በዓሉን ያከብሩት ጀመር። በዚህም ማርያም ደስ ተሰኝታ ወደእርሱ በመምጣት ማንም ሰው ያልለበሰውን ልብስና ከዚህ በፊት ሰው ተቀምጦበት የማያውቀውን ወንበር ሰጥታው በድጋሚ አመስግናው ተሰወረች ይላል ("ተኣምረ ማርያም" ነኛ ተኣምር ገጽ 14-15)።

በዚህ ክፍል ለመመልከት እንደሚቻለው ደቅስዮስ ተኣምረ ማርያምን ሰበሰበ ተብሎ የተጻፈ ቢሆንም፣ መልሶ ደግሞ ማርያም ይህን መጽሐፍ ስለጻፍህልኝ እንዳለችው ተገልጿል። ሰበሰበም ተባለ ጻፈ፣ መምህር ታሪኩ እንዳሉት ይህ ሥራ የተሠራው በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት (2ጴጥ. 1÷21) ሳይሆን በራሱ በደቅስዮስ ተነሣሽነት ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ደግሞ እርሷን ከመውደዱ የተነሣ የሚያደርገው ስለጠፋው ነው። ስለዚህ የእሷን ክብር እያበዛ ይጨምር ዘንድ ተነሣሣ። መጽሐፉ ላይ ከፍቅሩም ጽናት የተነሣ አስቦ እንጂ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ይህን ሥራ እንደሠራ የሚያወሳ ምንም ነገር የለም።

ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ያለው መቼ ነው? ተኣምረ ማርያምና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት የተጻፉትስ መቼ ነው? ተአምራትና ገድላት እንዲሁም ድርሳናት በእግዚአብሔር መንፈስ እንደተጻፉ ለማወቅ የሚያስችለንስ ምንድን ነው?

ተኣምረ ማርያም የተጻፈው ከ1426-1460 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ፣ ማለትም ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከእስጢፋኖሳውያን ጋር በወንጌል ምክንያት በነበረው አለመግባባት ምክንያት እንደ ነበር ይታወቃል። ምንም እንኳ ተኣምረ ማርያምን ጨምሮ ብዙዎች ይህን እውነት በመቃወም ከግብጽ እንደመጣና ወደግእዝ እንደተተረጎመ ቢናገሩም እውነታው ግን በንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ጊዜ መጻፉ ነው። የሚገርመው ነገር "እንዲህ ዓይነት ተኣምር ግብጽ ውስጥ አለመኖሩ ለአሥርና ለአሥራ ሦስት ዓመታት ያህል ቆይተው የመጡ መነኮሳት ማረጋገጣቸው ነው። ... የታሪኩ ሁለንተና እንደሚያስረዳው ተኣምሩ የተዘጋጀው እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ... አባ ሚካኤል አባ ገብርኤል የተባሉት ጳጳሳት በዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ናቸው" ("ይነጋል" መምህር ጽጌ ስጦታው፣ ገጽ 56-57)።

ለዚህም ምስክር ከሚሆኑት ነገሮች አንዱ "በሥዕሏም ፊት ስገዱ፤ ለሥዕሏ ያልሰገደ ግን ከቆመበት ቦታ ይጥፋ፤ ስም አጠራሩ አይታወቅ" ("ተኣምረ ማርያም" የዘውትር መቅድም ገጽ 5 ቁ. 35) የሚለው ነው። ይህ እርግማን አዘል ትእዛዝ ንጉሡ ዘርዐ ያዕቆብ ከእስጢፋኖሳውያን ጋር ስግደትን በተመለከተ በነበረው አለመግባባት ምክንያት የወጣ ትእዛዝ ነው። በመሠረቱ እንዲህ ዓይነቱ እርግማን ክርስቲያን ነኝ ከሚል ሰው የሚጠበቅ አይደለም። ክርስትና የሚያስተምረው የሚረግሟችሁን መርቁ ነው እንጂ፣ በሥዕል ፊት

ያልሰገዱ ሰዎች እርግማን ይገባቸዋልና እርገሟቸው አይደለም። ከክርስትና ትምህርት ጋር የማይሄድን ይህን መሰል መጽሐፍ ትክክል ነው ብሎ ማመን ከክርስትና ትምህርት ጋር አብሮ ለመሄድ ፈቃደኛ አለመሆን ነው።

ሌሎች ድርሳናትና ገድላትም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተጻፉ ናቸው እንጂ፣ ከጳውሎስ ቀደም ሲል የነበሩ አይደሉምና ሐዋርያው በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ ብሎ ከጠቀሳቸው መጻሕፍት ውስጥ አይደሉም።

በምድር ላይ ካሉት መጻሕፍት ሁሉ ይልቅ ብቻውን ትክክል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የእርሱን ያህል ሊከበር የሚገባውና የሰውን ሕይወት በመቀየርም በኩል ትልቁን ስፍራ ሊይዝ የሚችል መጽሐፍ ፈጽሞ የለም። አንዳንዶች በሰው ፈቃድና ስሜት የተጻፉትን መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሊያስተካክሉ ሲሞክሩ፣ ሌሎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እንከን አለበት በማለት የራሳቸውን ልቦለድ እንድንቀበላቸው ጥረት ያደርጋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የጽድቅ መልእክቱንና ታላቅነቱን ይዞ ይዘልቃል።

ተኣምረ ማርያም ለምን ተጻፈ?

ተኣምረ ማርያም ስለራሱ ሲናገር÷ "ይህ የሥርዓት መጽሐፍ የምስር ዕፃ ከሚሆን ከመዓልቃ ቦታ ከሐዋርያው ከማርቆስ መንበር የወጣ ነው" ሲል÷ ስለጻፉት ሰዎች ማንነት ሲገልጽ ደግሞ፡-

"የሠሩትም መምህራን እመቤታችን ዘወትር የምታነጋግራቸው ሃይማኖታቸው የቀና ምስጢርን የሚያስተምሩ ክቡራን የሚሆኑ

ሊቃነ ጳጳሳት ናቸው፡፡ በራእይ የምታነጋግራቸው ጊዜ አለ፤ በሕልም የምታነጋግራቸው ጊዜ አለ፤ ተገልጻም የምታነጋግራቸው ጊዜም አለ፡፡ እኒህም ድንቅ ድንቅ ተኣምራት የሚሠሩ አባ አብርሃም አባ ማርቆስ አባ ማቴዎስ ናቸው" ብሏል ("ተኣምረ ማርያም" መቅድም ቁ. 1-7 ገጽ 8)፡፡

መምህር ታሪኩ ግን የተኣምረ ማርያም ጸሓፊ ደቅስዮስ የሚባል ሰው ነው በማለት የደራሲነቱን መብት ለደቅስዮስ ብቻ ሰጥተዋል፡፡ ተኣምረ ማርያም ግን የጻፉኝ ሦስቱ ሰዎች ፣ ማለትም አባ አብርሃም፣ አባ ማርቆስ እና አባ ማቴዎስ ናቸው ብሏል፡፡

እዚህ ላይ ከሁለቱ አንዳቸው ራሳቸውን ማስተካከል አለባቸው፡፡ ስሕተታቸውን ካመኑ መምህር ታሪኩ ተሳስቻለሁ በማለት ሐሳባቸውን ማስተካከል ይኖርባቸዋል፤ አሊያ ተኣምረ ማርያም የጻፈኝ ደቅስዮስ ብቻ ነው ብሎ ትክክለኛው ደራሲው ማን እንደሆነ በግልጽ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

መምህር ታሪኩ ይህን በአግባቡ ሳይመልሱ በዘማሪ ኤፍሬም ላይ ያነጣጠረውን ትችታቸውን ወደማቅረብ ተሸጋግረዋል፡፡

"... የሥልጣን ጥማት ያለባቸው ነው ያለው? የሥልጣን ጥማት ያለባቸው ሰዎች ሕዝብን ለመግዛት ያመቻቸው ዘንድ፤ በተኣምር ነው እንዴ የሕዝብ አስተዳደር የሚካሄደው? በገድለ ተክለ ሃይማኖት ነው እንዴ የሕዝብ አስተዳደር እርምጃ ማካሄድ የሚቻለው? በገድለ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ በድርሳነ ሚካኤል፣ በዚህ ነው እንዴ የኢትዮጵያ ነገሥታት የኢትዮጵያ አባቶች ሕዝብን ሲያስተዳድሩ የነበሩት?" (17፡57-18፡31 ደቂቃ)፡፡

በማለት ተኣምረ ማርያም ለምን እንደተጻፈ የሚመሰክረውን ታሪካዊ ማስረጃ ወደጎን ገሸሽ ለማድረግ ሙከራ አድርገዋል፡፡ ከዘርዐ ያዕቆብ የንግሥና ዘመን ቀደም ብለው የነበሩትና በመልካም ትምህርታቸው ተመስክሮላቸው በሰላም ሲኖሩ የነበሩት እስጢፋኖስና ተክታዮቹ፥ ሰማይንና ምድርን ለሠራ ለእግዚአብሔር እንጂ ለንጉሥም ሆነ ለምስል (ለመስቀሉ ቅርጽና ለማርያም ሥዕል) አንሰግድም በማለታቸው ንጉሡ ሌሎች እንዲፈሩ በማለት አፍንጫቸውና ምላሳቸው እንዲቆረጥ ማዘዙን ተኣምረ ማርያም ዘግቧል ("ተኣምረ ማርያም" 24ኛ ተኣምር ቁ. 36-37 ገጽ 96)፡፡ ንጉሡ በእስጢፋኖሳውያን ላይ የፈጸመውን የጭካኔ ተግባር በደማቅ ቀለም በተኣምረ ማርያም ላይ ማጻፉ ከቶ ለምን ይሆን? የፈጸመው በግፍ የተሞላ ቅጣት ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆንና ሁሉም ሰጥ ለጥ ብሎ ለእርሱ እየሰገደ እንዲኖር፥ በሌላ አገላለጽ ለአገዛዝ እንዲመቸው ያደረገው አይደለምን?

በአጠቃላይ ተኣምረ ማርያም በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ፍላጎት የተጻፈ ለመሆኑ የታሪክ መዛግብት ይመሰክራሉ፡፡ ከዚህ ሌላ የታሪኩ አወቃቀርና መልእክቱ ከየት መጣውን ለመደበቅ የተደረገውን ጥረት መፈተሽ÷ መጽሐፉ መቼ ተጻፈ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

"ጳውሎስ እንዳለ"

"እስኪ ተኣምረ ማርያምን እባካችሁ ገዝታችሁ እቤት ቁጭ ብላችሁ አንብቡት" የሚሉት መምህር ታሪኩ ገድላት ተኣምራትና ድርሳናት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ፍጹም ስምምነት ያላቸው ከመሆኑም በላይ÷ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ያላቸው ናቸው ይላሉ፡፡

"... የትኛው ምዕራፍ ነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ውጪ ሐሳብ ይዞ የሚገኝ? የሚገርማችሁ እያንዳንዱን ምዕራፍ ብትመለከቱት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆነ ሐሳብ የለውም፡፡ ተኣምረ ማርያም ብቻ አይደለም ሌሎች ገድላት፣ ድርሳናትን ብትመለከቱ 'በከመ ይቤ ጳውሎስ፤ - ጳውሎስ እንዳለ፣ በከመ ይቤ ማቴዎስ፣ በከመ ይቤ እግዚእነ፤ ጌታችን እንዳለ፣ ማቴዎስ እንደጻፈው' እያሉ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው የቤተ ክርስቲያን አዋልድ መጻሕፍት የተጻፉት" (ነ፡53-24፡43 ደቂቃ)፡፡

እርግጥ ነው፤ አዋልድ መጻሕፍት ተቀባይነትን እንዲያገኙ መጽሐፍ ቅዱሳውያን ጥቅሶችን እንደ ፈርጥ መጠቀማቸው የተለመደ ነገር ነው፡፡ ደራሲዎቹ ይህን የሚያደርጉበት አንዱ ምክንያትም የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ለልቦለዳዊ ድርሰታቸው ማጣፈጫ ለማድረግ ነው፡፡ 'ጳውሎስ እንዲህ እንዳለ፣ ጴጥሮስ እንደተናገረ ...' ካሉ በኋላ የልባቸውን መሻት ይጽፉሉ እንጂ የመጽሐፍ ቅዱሱን እውነት ይዘው እስከመጨረሻው አይዘልቁም፡፡ ለምሳሌ፡- ከድርሳነ ሚካኤል ላይ ሁለት ነገሮችን ብቻ እንመልከት፤

- በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በኢያሱ ፊት ማንነቱ ያልተገለጸ መልአክ ቆሞ እንደነበረና ኢያሱም በፊቱ የቆመው መልአክ ሰው መስሎት "ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን?" (ኢያ. 5፡13) እንዳለው ተጽፏል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የዚህን መልአክ ማንነት በግልጽ ባያስቀምጥም በቁጥር 15 ላይ "አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ" ብሎ ከማዘዙና በምዕራፍ 6

ቍጥር 2 ላይ "እግዚአብሔርም ኢያሱን አለው" ተብሎ ከተጻፈው አንጻር፥ መልአክ ሳይሆን ከያዕቆብ ጋር በአርኣያ መልአክ ሲታገለው የነበረው አምላክ እስራኤል እንደሆነ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ የድርሳነ ሚካኤል ደራሲ ግን ይህ መልአክ ተብሎ የተገለጸው ሚካኤል ነው እንጂ ሌላ ማንም አይደለም በማለት መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሶ ሊሞግት ሞክሯል፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጻፈውን "በዚህችም ቀን አማሌቅን በእጅህ እጥለዋለሁ፡፡ በኢያሪኮም ላይ አነግሥአለሁ" ሲል ሚካኤል እንደተናገረ በማስመሰል ጽፏል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ግን ኢያሪኮንና ንጉሥዋን በእጅህ ሰጥቼአለሁ ነው ("ድርሳነ ሚካኤል" የጳጉሜ ድርሳን፣ ገጽ 75-77)፡፡

- መምህር ታሪኩ ሐዋርያት ስለማርያም አስተምረዋል በማለት በእርግጠኝነት ለማስተማር ጥረት አድርገዋል፡፡ ድርሳነ ሚካኤል ላይም ሐዋርያት ስለ ሚካኤል አስተምረዋል የሚል ተጽፏል፡፡ ስለዚህ ስለሚካኤልም አስተምረዋል ሊባል ነው? ወይስ ስለማርያም ብቻ ነው ያስተማሩት? የሚል ጥያቄ ይነሣል (ድርሳነ ሚካኤል የጳጉሜ ድርሳን ገጽ 501)፡፡ መቼም መጽሐፍ ቅዱስ ስለድንግል ማርያምም ሆነ ስለቅዱስ ሚካኤል በተጻፈው ውስጥ ዐላማው የእግዚአብሔርን ሥራ መግለጥ እንጂ እነርሱን መስበክ አይደለም፤ ወይም ደግም በዚህ መነሻነት በቅዱሳን ስም እነርሱ ያላደረጉትንና የማያውቁትን ታሪክ ፈጥረን የፈለግነውን እንድንጽፍ በር ለመክፈት አይደለም፡፡

አንድን ጽሑፍ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት የያዘው መልእክት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የተስማማ ሆኖ መገኘት

አለበት፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ስለጠቀሰና እንዲህ ተብሎ ተጽፏል ስለአለ ብቻ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊባል አይችልም፡፡ ስለዚህ ገድላት፣ ድርሳናትና የተኣምር መጻሕፍትም እነርሱ የሚፈልጉትን መልእክት እንዳሻቸው እየጻፉ ‘በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ’ ብለው ስለጀመሩና መጽሐፍ ቅዱስን ስለጠቀሱ መጽሐፍ ቅዱሳውያን ናቸው ወደሚል ድምዳሜ አያደርስም፡፡

"ይገለጣ መጽሐፍ ቅዱስ"

የእግዚአብሔር መልአክ ገብርኤል ወደማርያም ተልኮ በመጣ ጊዜ÷ የተናገራቸው ቃላት በዚህ ዘመን ለማርያም ስግደት ይገባታል፣ ምስጋና ይገባታል፣ … ለማለት ትልቅ ምክንያት ሆኗል፡፡ መምህር ታሪኩም የገብርኤልን ንግግር መሠረት በማድረግ፡-

> "ገብርኤል እመቤታችንን አላመሰገናትም? አላወደሳትም? ይገለጣ መጽሐፍ ቅዱስ! ‘ወበሳድስ ወርኅ ተፈነወ ገብርኤል መልአክ እምኀበ እግዚአብሔር’ በስድስተኛው ወር ከእግዚአብሔር ዘንድ መልአኩ ገብርኤል ተልኮ ወደናዝሬት ገሊላ መጣ ወደእመቤታችን ‘ቦአ ኀቤሃ ወይቤላ ተፈሥሒ ፍሥሕት አ ምልእተ ጸጋ ቡርክት አንቲ እምአንስት ወብሩክ ፍሬ ከርስኪ’፤ ‘ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ <u>ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ</u> አንቺ የተባረክሽ ነሽ’ ምስጋና ነው ይሄ፤ ውዳሴ ነው ይሄ፤ አኮቴት ክብር ነው፤ መልአኩ ለእመቤታችን ያቀረበው፡፡ የእመቤታችንን ስም በአክብሮት ጠርቶ ነው ‘ቡርክት አንቲ እም

አንስት' 'በዓለም ካሉ ሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ ቡርክት ነሽ' ምን ማለት ነው ቡርክት ነሽ ማለቱ? መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የለብሽም፤ ንጽሐ ሥጋ ነጽሐ ነፍስ አለሽ፤ ማንም ሴት ግን ቡርክት አልተባለችም፤ አንተ ኤልሳቤጥ አልተባለችም፤ ዲቦራ፣ ሣራ፣ ራሔል፣ አስቴር፣ ርብቃ፣ ሔዋን ራሷ አልተባለችም፤ እመቤታችን ብቻ ከሴቶች ተለይተሽ ቡርክት ነሽ፤ ሌሎቹ የውርስ ኃጢአት አለባቸው፡፡ እመቤታችን ግን ከውርስ ኃጢአት ንጽሕት ነች፡፡ ለዚህ ነው ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ ብሩክት ነሽ" የተባለችው ሲሉ አስተምረዋል (38፡20-40፡00 ደቂቃ)፡፡

መምህር÷ ገብርኤል ለማርያም ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ ነው ያላት? እርስዎ እንዳሉት ይገለጣ መጽሐፍ ቅዱስ! "በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሆነው የሴፍ ለሚባል ሰው ወደታጨች ወደአንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ÷ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ፡፡ መልአኩም ወደ እርሷ ገብቶ ደስ ይበልሽ÷ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት" (ሉቃ. ፩÷26-28)፡፡ ታዲያ መጽሐፉ እንዲህ ከሆነ የሚለው እርስዎ ከአንድም አራት ጊዜ (በሌሎችም ቦታዎች የተናገሩትን ትተን)÷ ያልተጻፈውን እንደተጻፈ አድርገው ለመናገር ለምን ፈለጉ? ይህን በማድረግዎ እግዚአብሔርን እያገለገሉ መስሎዎ ይሆን?

መምህር÷ ይህ ብቻ አይደለም፤ ይህን ጥቅስ መሠረት አድርገው ማርያም የውርስ ኃጢአት እንደሌለባት አስተምረዋል፡፡ ይህ ምንባብ ግን ለዚህ ትምህርትዎ መነሻ ሊሆን የሚችል መልእክት የለውም፡፡ ማርያም

በእግዚአብሔር ዘንድ የመመረጧ ምስጢር ራሱ ግሩም የሆነ የእግዚአብሔር ምስጢር ነው፡፡ ነገር ግን የተመረጠችው ቅድስት ስለሆነች ነው፤ የውርስ ኃጢአት ያልነካት ንጽሕት ዘር ስለሆነች ነው ለማለት የሚያበቃ ምንም መነሻ የለም፡፡

መምህር ታሪኩ መቼም አገልጋይ እንደመሆንዎ መጻሕፍትን ያነባሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ "ትምህርተ መለኮት" የተሰኘውና በዐሥራት ገብረ ማርያም የተዘጋጀው መጽሐፍ÷ "በቤተ ክርስቲያን እምነት መሠረት በሉቃስ ወንጌል ም. ፩ ቁ. 38 ላይ የመልአኩን ብሥራት ተቀብላ 'እነሆኝ የጌታ ባርያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ' ብላ እምነቷን በእግዚአብሔር ላይ ባሳረፈች ጊዜ÷ ጌታን ከመውለዷ በፊት መንፈስ ቅዱስ እመቤታችንን ቀድሶና አንጽቶ የጥንቱን የአዳምን ኃጢአት አስወግዶላታል" የሚለውን ምስክርነት እንዴት ያዩታል? በጥር ማርያም ዚቅ ላይ ደግሞ "አንጺሖ ሥጋሃ ጎደረ ላዕሌሃ" ማለትም "ሥጋዋን አንጽቶ በእርሷ ላይ አደረ" የሚለውንስ? እርስዎ ብዙ ያሉለት ተኣምረ ማርያም እንኳ "ከኃጢአት በቀር ሥጋዋን ለተዋሐደ ለወልድም ምስጋና ይገባዋል" ብሏል፤ ይህንንም አላነበቡት ይሆን? ("ትምህርተ መለኮት" ገጽ 96፡፡ "ይነጋል" መምህር ጽጌ ስጦታው ገጽ 34-36፡፡ "የዘመናት እንቆቅልሽ ሲፈታ" መሪጌታ ሠረቀ ብርሃን ዘወንጌል ገጽ 29)፡፡

በእርግጥ ሥጋዋን አንጽቶ በእርሷ አደረ ሲባል ከእርሷ ኀጢአት ተወገደ ማለት እንዳልሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም ጌታ ሳይሰቀልና ደሙ ሳይፈስ የኀጢአት ስርየት የለምና (ዕብ. 9÷22)፡፡ ነገር ግን ይህ÷ "መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል" (ሉቃ. ፩÷35) በተባለው መሠረት መንፈስ ቅዱስ ቃል

ከእርሷ የሚዋሐደውን ሥጋ ከፍሏል፤ አንጽቷል፤ አዋሕዷል ማለት እንደሆነ አርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ያብራራሉ (ቅዳሴ አንድምታ ዘሠለሥቱ ምእት ገጽ 274)።

በመጨረሻም መምህር ታሪኩ፥ ገብርኤል ማርያምን እንዳመሰገናት አስተምረዋል። የመልአኩን ንግግር ለማርያም የቀረበ ምስጋና ነው ከማለት ብሥራቱን ቀድመው የተነገሩ የደስታ መግለጫ ቃላት ናቸው ቢባሉ ተስማሚ ይመስላሉ። ቃላቱ፡-

- ደስ ይበልሽ
- ጸጋ የሞላብሽ ሆይ
- ጌታ ከአንቺ ጋር ነው
- አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ

የሚሉ ናቸው። ታዲያ እንዴት ሆነው ቢነበቡ ነው እነዚህ የደስታ መግለጫ ቃላት ለማርያም የቀረቡ ምስጋና ናቸው የሚባሉት?

ፍጥረት ሁሉ ማርያምን ለማመስገን ተፈጠረ

እንደ ገብርኤል ሁሉ ኤልሳቤጥም አመስግናታለችና እኛም እርሷን አብነት አድርገን እናመሰግናታለን የሚል ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች አሉ። መምህር ታሪኩም ይህን ሐሳብ እንዲህ ነው ያቀረቡት፡-

> "'ፍጥረት ሁሉ እመቤታችንን ለማመስገን ተፈጠረ' አለ ቅዱስ ደቅስዮስ። እውነቱን ነው መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን አብነት፣ ሞዴል አድርገው ያመሰግናሉ የአዳም ልጆች ደግሞ እኛ ማንን ምሳሌ አብነት አድርገን እናመሰግናታለን? ኤልሳቤጥን" (40፡25-41፡27 ደቂቃ)።

ገብርኤል ለማርያም ያቀረበውን ሰላምታና የደስታ መግለጫ ቃላት÷ ኤልሳቤጥም ያቀረበችላትን ሰላምታና አድናቆት መነሻ በማድረግ ዛሬ ለማርያም ምስጋና ማቅረብ ይገባል ማለት መሠረት የለሽ አስተምህሮ ነው፡፡ ሁለቱም ከድንግል ማርያም ጋር ፊት ለፊት ተገናኝተው ያቀረቧቸውን የደስታ መግለጫና የሰላምታ ቃላት÷ መነሻ በማድረግ እኛም እርሷን በአካለ ሥጋ ባላገኘንበት ሁኔታ ምስጋና ልናቀርብላት ይገባል ማለት ፍጹም የማያስኬድ ነገር ነው፡፡ እርሷ ራሷ "እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" መምህር ታሪኩና መሰሎቻቸው እንደሚሉት ትውልድ ሁሉ ምስጋና ያቀርቡልኛል ለማለት አይደለም፡፡ ጌታ በእርሷ ከሠራው ታላቅ ሥራ የተነሣ ለዚህ ዕድል የተመረጠች ድንግል ማርያም ብፅዕት ማለትም ደስ የተሰኘች ወይም የከበረች ናት በማለት አድናቆቱን ይገልጻል ማለት ነው እንጂ እግዚአብሔር በሚመሰገንበት አኳኋን ማርያምን ሲያመሰግን ይኖራል ማለት አይደለም፡፡

"ፍጥረት ሁሉ እመቤታችንን ለማመስገን ተፈጠረ" የሚለውን ያህል አስተምህሮኣዊ ስሕተት ፈጽሞ የለም፡፡ ይህን ትልቅ ስሕተት ትክክል ነው ብሎ ከማስተማር የከበደ ሰዎችን ወደስሕተት መምራትም የለም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ፍጥረቱን የፈጠረው ለራሱ ክብር እንደሆነ ይናገራል (ምሳ. 16÷4)፡፡ የፍጥረትን ውዳሴና ቅዳሴ ሊቀበል የሚገባውም እርሱ እንደሆነ ሲመሰክር "ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው ከዘላለም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ፡- ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና

ስለፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል" ነው የሚለው (ራእይ. 4÷10-11)።

መምህር ታሪኩ ያላስተዋሉት ነገር ቢኖር ተኣምረ ማርያም የሚለው ፍጥረት ሁሉ ማርያምን ያመሰግናል ሳይሆን እመቤታችንን ለማመስገን ተፈጠረ ነው። ፍጥረት ፍጥረትን ለማመስገን ተፈጠረ የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ፈጽሞ የለም።

ሰው ፈጣሪውን የሚያመሰግነው የተፈጠረበት ዐላማ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር የዓለማት ሁሉ ፈጣሪ ነው፤ ሰውንም በመልኩና በምሳሌው ፈጥሮታል። ከዚህ ሁሉ በላይ በበደልን ጊዜ እኛን ለማዳን አንድ ልጁን ቤዛ አድርጎ ሰጥቷል፤ ስለዚህ ስለ አምላክነቱና ስላደረገልንም ነገር ሊመሰገንና ውዳሴ ሊቀርብለት ይገባል። ማርያም በፍጥረት ሥራ ውስጥ ያደረገችው አስተዋፅኦ የለም፤ እርሷ ራሷ ፍጡር ናት፤ ስለዚህ ፍጥረት ሊያመሰግናት ይገባል የሚባለው እንዴት ነው? ዓለምን በማዳን በኩልም ቢሆን እርሱ እግዚአብሔር መረጣት እንጂ እርሷ ከራሷ ያደረገችው ምንም ነገር የለም፤ በመሆኑም በዚህ ሁሉ ብቻውን ሊመሰገን የሚገባው እርሱ ነው።

ያዳነን የማርያም ሥጋ ነው

ማርያምን ፍጥረት ሁሉ ሊያመሰግናት ያስፈለገበትን ምክንያት መምህር ታሪኩ ሲያስረዱ፡-

> "እመቤታችን በእርግጥ ምስጋና ይገባታል ክብር ይገባታል ... ምስጋና ይገባታል፤ አካላዊ ቃልን ለማስተናገድ እሳተ መለኮትን በማኅፀኗ ለመሸከም ዓለም ሁሉ እንዲድን የእርሷ ሥጋ

ምክንያት ሆኗልና ለድንግል ማርያም ምስጋና ይገባታል" ብለዋል (41፡35-42፡30 ደቂቃ)።

እርግጥ ነው ጌታችን ሰው ሆኖ የተወለደው ከማርያም ነው። ከእርሷ በነሣው ሥጋም ቤዛ ሆኖ ሞቷል። መከራ የተቀበለውና የሞተው ክርስቶስ ሆኖ ሳለ ክርስቶስ ሥጋውን ያመጣው ከማርያም ነው እንጂ ከየትም አላመጣውምና የማርያም ሥጋ ነው የተሰቀለው ማለት ምክንያታዊነት ይጎድለዋል። እንዲህ ማሰብ ፍጹም አላዋቂነት ነው። ማንም በትክክል የሚያስብ ሰው ይህን ሊቀበል ቀርቶ አስቦም አያውቅም። ይህ ማለት እኮ በዓለማችን ታላላቅና ድንቅ ሥራን የሠሩ ሰዎች ቢኖሩ÷ ያ ታላቅ ሥራ የእነርሱ ሳይሆን የእናቶቻቸው ነው የማለት ያህል ነው። የታሪክ ሠሪ ሰው እናትም ብትሆን÷ ይህን ልጄ ሠራ ብላ በልጇ ሥራ ትደሰታለች እንጂ እርሱ ቢሠራውም ከእኔ በወሰደው ሥጋ ነውና የሠራው እኔ ነኝ ያን ታሪክ የፈጸምሁት ስትል ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።

ለምሳሌ መምህር ታሪኩ አሁን ያቀረቡት የተሳሳተ መልእክት የእርሳቸው እንጂ የእናታቸው ነው እንደማይባል ሁሉ÷ ክርስቶስም በሥጋውና በደሙ ለድኅነተ ዓለም የሠራው ሥራ የእርሱ እንጂ የማርያም ሥራ ነው ሊባል አይቻልም። መጽሐፍ ቅዱስም ይህን ሲያረጋግጥ፡-

- "<u>እርሱም በሥጋው</u> ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ" (ዕብ. 5÷7)።
- "በዚህም ፈቃድ <u>የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ</u> አንድ ጊዜ በማቅረብ ተቀድሰናል" (ዕብ. 10÷10)።

- "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ በመረቀልን በአዲስና በሕያው መንገድ ወደቅድስት <u>በኢየሱስ ደም</u> በመጋረጃው ማለት <u>በሥጋው</u> በኩል እንድንገባ ድፍረት ስላለን..." (ዕብ. 10÷19-20)፡፡
- "ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ <u>በገዛ ደሙ</u> ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጪ መከራን ተቀበለ" (ዕብ. 13÷12) ይላል፡፡

ቃሉ 'በገዛ ደሙ' 'በሥጋው' እያለ 'አይደለም የኢየሱስ ክርስቶስ *ሥጋ* ሳይሆን የማርያም *ሥጋ* ነው' ብሎ ከመጽሐፍ ቅዱስ *ጋር* ሙግት መግጠም ምን ይባላል? የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንኳን የማርያም *ሥጋ* ተሰቀለ የሚል ቀርቶ ከማርያም በለበሰው *ሥጋ* የሚል አገላለጽን አልተጠቀመም፡፡ *ያ ሥጋ* የእርሱ ገንዘብ ሆኗልና ከዚያ በኋላ እርሱ ብቻ እንጂ እናቱ ልትጠራበት አትችልም፡፡

ከዚሁ ሐሳብ *ጋር* በተያያዘ መምህሩ፡-

> "የዓለሙን መድኅን ለሰጠች ለእመቤታችንማ ብንዘምር፣ ብንቀድስ፣ ማኅሌት ብንቆም፣ ሰዓታት ብናደርስ፣ ሳንባችን ከጀርባችን እስኪጣበቅ ድረስ ለክብሯ ብንመሰክር ያንስባታል እንጂ አይበዛባትም ክብር ለድንግል ማርያም ይሁን!" (44፡40-45፡00 ደቂቃ) ሲሉ ያቀረቡት ትምህርትም አለ፡፡

ጌታ እግዚአብሔር ይቅር ይበለን! በእውነት ይህ እግዚአብሔርን የሚያስቀና ክፉ *ሥራ* ነው፡፡ ወይም የእግዚአብሔርን የሥራ ድርሻ ለማርያም መስጠት ነው፡፡ አንድያ ልጁን ለዓለም እስከመስጠት ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወደደ የተባለው እግዚአብሔር ነው እንጂ ድንግል ማርያም አይደለችም (ዮሐ. 3÷16)፡፡ ድንግል ማርያም የጌታ እናት ትሆን ዘንድ ተመረጠች እንጂ÷ የዓለምን መድኅን ሰጠች ተብሎ ሊነገርም

አይገባም፤ ይህ አነጋገር ትልቅ ድፍረት ነውና መምህር ንስሓ እንዲገቡ እግዚአብሔር ይርዳዎ!

ባለውለታችን ማን ነው?

አንድ ሰው ስጦታን በሰው በኩል ቢልክልዎ ማንኛው ነው ባለውለታዎ? ስጦታውን የላከልዎ ወይስ ስጦታውን ይዞልዎ የመጣው? ምንም ቢሆን መልእክተኛው ሳይሆን ላኪው እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡ ማርያም ለዓለም ድኅነት እግዚአብሔር አሳልፎ የሰጠውን ጌታ ወልዳለች፡፡ ይህን በምሳሌው መሠረት እንየው ከተባለ ስጦታውን የላከልን እግዚአብሔር ነው፡፡ ስጦታውን ያመጣችው ደግሞ ማርያም ናት ማለት እንችላለን፡፡ ስጦታውን ከራሷ አምጥታ አልሰጠችንምና ስጦታን ስለላከልን ምስጋና የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

መምህር ታሪኩ ግን ሞታችን ተወግዶ ሕይወትን ያገኘነው በኢየሱስ ሳይሆን በማርያም ነው እስከማለት ደርሰዋል፡፡

> "[ማርያም] ባለውለታችን ነች፤ ሞት የመጣብን በማን ነው? በሔዋን አይደለም? ሕይወትስ የተገኘው በማን ነው? በድንግል፡፡ የነነት ደጅ የተዘጋው በማን ነው? በሔዋን የተከፈተው ግን በማን ነው? በድንግል ማርያም ‘በእንተ ሔዋን ተዐፅወ ኖኅተ ነነት ወበእንተ ማርያም ድንግል ተርኅወ ለነ ዳግመ’ በሔዋን ምክንያት የተዘጋው የነነት ደጃፍ በድንግል ማርያም ምክንያት … ተከፈተልን" (45፡38-46፡16 ደቂቃ)፡፡

መምህር ታሪኩ በዚህ ውስጥ ‘ማርያም ባለውለታችን ነች’ ሲሉ÷ ውለታዋ ምን እንደሆነ ውዳሴ ማርያምን ጠቅሰው ሕይወትን

ማስገኘቷና የተዘጋውን የገነት ደጅ ማስከፈቷ ነው ብለዋል። የልጇን ሥራ ለእርሷ እንስጥ ካልተባለ በቀር÷ ይህን ሥራ የሠራው በሥጋ የወለደቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንጂ እርሷ አይደለችም።

ኢየሱስን ለመውለድ በመመረጧ "እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደቃልህ ይሁንልኝ" ብላ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሷን ከማስገዛት በቀር÷ ያደረገችው ነገር የለም። ጉዳዩ ሁሉ ከእርሷ ውጪ እንደሆነ የሚያሳየው የማርያም ቃልም "ይሁንልኝ" የሚለው ነው (ሉቃ. ፩÷38)። አንዳንድ አባቶች እንደሚሉት ከሆነ ይህ የማርያም ቃል የራሷንም ሕይወት የቀየረ ነው ("ትምህርተ መለኮት" ዐሥራት ገብረ ማርያም ገጽ 96)።

እርሷ ራሷ ውለታ የተዋለላት ነችና÷ "ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች÷ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤ የባሪያይቱን ውርደት ተመልከቶአልና" በማለት ባለውለታዋን ያከበረች ሴት ናት (ሉቃ. ፩÷47)።

መምህር ታሪኩ የክርስቶስን የቤዛነት ሥራ ለእናቱ በመስጠት ሥራቸውን በዚህ ብቻ አላቆሙም። መጽሐፍ ቅዱስ "በአንዱ ሰው (በአዳም) አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደሆኑ÷ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ (በክርስቶስ) መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ" የሚለውን አልቀበልም በሚል መንፈስ ይመስላል፡-

> "ሔዋን ዕፀ በለስን በልታ፣ ምክረ ከይሲን ሰምታ ትእዛዘ እግዚአብሔርን ጥሳ፣ በትውልድ ላይ ሞት አምጥታ ነበር። እመቤታችን ግን የመላእክት ብሥራት ሰምታ፣ ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቃ፣ በንጽሕና በቅድስና አሸብርቃ፣ የዓለምን ሁሉ መድኀኒት ሰጥታ፣ የተዘጋው ገነት እንዲከፈት

አድርጋለች፤ ለሐናና ለኢያቄም ልጅ ለማርያም ምስጋናና ውዳሴ ይድረሳት" (46፡15-46፡45 ደቂቃ) ያሉት፡፡

መምህር÷ ዘማሪ ኤፍሬምን ያበሳጨ መስሎዎ ለማርያም የሠዉት ውዳሴና ምስጋና እግዚአብሔርን የሚያስቀናውና የሚያስቈጣው እንደሆነ አላስተዋሉ ይሆን? "አዳም ለኃጢአትና ለሞት ወደዓለም መምጣት ምክንያት ሆነ፤ ክርስቶስ ግን ጽድቅንና ሕይወትን አመጣ" (ኢ.መ.ት ገጽ 1714)፡፡ መምህር÷ ተሳስቷል እያሉ ያለው ሰውን ነው ወይስ መጽሐፍ ቅዱስን? እንደአያያዝዎ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስን በውዳሴ ማርያም እያስተካከሉት መሆኑን ተገንዝበው የአሮጊቶችን ተረት ከመሰለው ትምህርት ወደእግዚአብሔር ቃል እንዲመለሱ ይመክራሉ፡፡

ሐዋርያት ስለማርያም መስበካቸው

በተኣምረ ማርያም ላይ÷ "አባቶቻችን ሐዋርያትስ ልሳነ ዕፍረት ክቡር ጳውሎስ እንደተናገረ በዚህ ዓለም እንደ ጥንግ የሆኑ ስለማን ነው? ስለማን በእግር ብረት አጽንተው አሰሯቸው? ከዓላውያን መኳንንት ነገሥታት ዘንድ ጠብ ክርክር ባለበት አደባባይ ስለማን መከራ አጸኑባቸው? <u>ብሎ እንደተናገረ</u> ሰውን ሁሉ ባጠመቁ ጊዜ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች የክብርት እመቤታችንን ነገር በማስተማር አይደለምን? የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም ነገር በማስተማር አይደለምን?" ("ተኣምረ ማርያም" ምዕራፍ 6 ቁ. 25-28 ገጽ. 27) የሚለውን ለማብራራት ዐቅም ያነሳቸው መምህር ታሪኩ ማጣፊያው ሲያጥራቸው÷ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ስለማርያም እንዴት

አልሰበኩም ይባላል? በጣም ሰብከዋል እንጂ በማለት ማስረጃ ሳያቀርቡ ለማደናገር ከጥቅስ ወደጥቅስ መዝለልን ዘዴ ብለው ይዘዋል፡፡

መምህር ታሪኩ የጠቀሱትን ጥቅስ ከማየታችን በፊት÷ ሊያስተምሩ የሞከሩትና ተኣምረ ማርያም የሚለው አልስማማ እንዳሉ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ መምህሩ፡-

> "ሰውዬው ለምንድን ነው ግን እንደ አረም አንድ ቃል ብቻ መዘ የሚያወጣው? ሐዋርያት መከራ ደረሰባቸው ያለው ተኣምረ ማርያም ላይ ስለማርያም በመናገራቸው ብቻ ነው እንዴ? አይደለም፤ ሦስት ነገሮችን በማስተማራቸው ነው፤ አንደኛ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስበካቸው፤ ሁለተኛ በማጥመቃቸው አሕዛብን በማጥመቃቸው፤ ሦስተኛ ስለማርያም ነገር በመናገራቸው አለቀ፡፡ … አሕዛብን በሥላሴ ስም በክርስቶስ ስም በማጥመቃቸው ወደወጎኒ ወርደዋል፤ እናምናለን ስለእመቤታችን አልሰበኩም ብሏል አስረግጠን እንናገራለን እነጴጥሮስ፣ እነእንድርያስ እነቶማስ፣ እነሉቃስ እነዮሐንስ ሁሉም ስለእመቤታችን ክብር መስክረዋል መጽሐፍ ቅዱስ ይመስክር" ብለዋል (53፡39-55፡09 ደቂቃ)፡፡

እርሳቸው ከጥቅስ ውስጥ አንድ ቃል ብቻ መዝዘ ማውጣት ትክክል እንዳልሆነ ሲናገሩ÷ እውነታቸውን ነው በማለት ሙሉውን የተኣምረ ማርያም ክፍል ለማንበብ ሞክሬአለሁ፡፡ መጽሐፉ የሚናገረው ዮሐንስና ጴጥሮስ ወደቤተ መቅደስ ሲገቡ በር ላይ አግኝተዉት የፈወሱትን ሰው ተከትሎ የመጣባቸውን መከራ ነው፡፡ ከዚህም በኋላ በድጋሚ በዚህ ስም (በክርስቶስ ስም) እንዳታስተምሩ ተብለው ተገርፈው መለቀቃቸውን ይናገራል፡፡ በዚህ ክፍል ስለጥምቀትና ስለማርያም

አልተነገረም፡፡ ሙሉውን አንብቡ ከማለት ራሳቸው አስቀድሞ ሙሉውን አንብበው ቢሆን ኖሮ÷ የተኣምረ ማርያም ዘገባ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ታሪክ ጋር አብሮ እንደማይሄድ አገናዝበው ቢሆን ኑሮ÷ በዚህ ጉዳይ ላይ የትምህርት ርእስ ይዘው ለመስበክ ባልደፈሩም ነበር፡፡

መምህር ታሪኩ ተኣምረ ማርያም ሐዋርያት በማርያም ስም አስተምረው እንደነበረ የተናገረውን ከማሳየት ይልቅ÷ በመጽሐፍ ቅዱስ የማርያም ስም የተጠቀሰበትን ክፍል ተውሰው ‘ይኸው ስለማርያም እንዴት አላስተምሩም ይባላል፤ ይኸው አስተምረው የለም እንዴ!’ ብለዋል፡፡ ለመሆኑ ሐዋርያት በየትኛው ክፍል ላይ ነው ሥራዬ ብለው ስለማርያም ያስተማሩት? መምህር ታሪኩ ግን የሚከተሉትን ጥቅሶች እንደማስረጃ ያቀርቧቸዋል፡፡

"እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች" (ማቴ. ፩÷18) የሚለው አንዱ ማስረጃቸው ነው፡፡ በዚህ መነሻነት ማቴዎስ ማርያም ‘በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንደወለደችው ሰብኳል’ ወደሚል ድምዳሜ ደርሰዋል፡፡ እውን ማቴዎስ ይህን የጻፈው ስለማርያም ድንግልና ለመስበክ አስቦ ነውን? ኢየሱስ ስለተፀነሰበት÷ ወይም ማርያም ኢየሱስን ስለፀነሰችበት ሁኔታ ለመናገር አይደለምን? ስለዚህ ማእከላዊ ሐሳቡ ኢየሱስ እንጂ ማርያም አይደለችም፡፡

ቀጣዩ ማስረጃቸው ደግሞ ሉቃ. ፩÷28 ላይ "መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ፡- ደስ ይበልሽ÷ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ÷ ጌታ ካንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት" የሚለው ቃል ነው፡፡ ይህን ተተግነው "ከእናትዋ ማኅፀን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ጠብቋታል" በማለት

ሉቃስ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ንጽሕት ናት ብሎ እንደሰበከ አድርገው አስተምረዋል፡፡ ነገር ግን በዚሁ ንግግራቸው ላይ ቀደም ብለው "ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ንጹሕ ስለሆነ አስቀድሞ ማደሪያውን አነጻ" ያሉትን ያስተዋሉት አይመስልም (ነ፡02፡20-ነ፡06፡5ነ ደቂቃ)፡፡ መቼም መንጻት የሚያስፈልገው ንጹሕ ያልሆነ ነገር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

እርስ በርሱ ከሚጋጨው የእርሳቸው ትምህርት በላይ ግን የሉቃስን ጥቅስ አለንባቡ እንደተረጎሙት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከሴቶች መካከል የተባረከሽ ነሽ የሚለው ንባብ እንዴት ሆኖ ቢተረጎም ነው "ከእናትዋ ማሕፀን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ጠብቋታል"÷ እንዲሁም ‘መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የለባትም’ ወደሚል ምስጢር የሚደረሰው? ይህ በእውነት ያልተጻፈውን ማንበብ ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ መምህሩ ሐዋርያት ስለማርያም አስተምረዋል በማለት ያቀረቡት ማስረጃ ዮሐ. 2÷3ን ነው፡፡ በዚህ ክፍል ላይ "የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት፡- የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው" የሚለውን በመጥቀስ፡-

> "ለምን ተጻፈ ይሄ ቃል? ይህቺ ዓርፍተ ነገር ለምን ተጻፈች? ሁላችሁም ታውቃላችሁ በቃና ዘገሊላ ውሃ ወደወይን ጠጅ ኢየሱስ ለወጠ ብሎ እኮ ማቆም ይቻላል፡፡ ዮሐንስ የማርያምን ንግግር ማስገባት ለምን አስፈለገው? የወይን ጠጅ ባለቀ ጊዜ እናቱ ኢየሱስን መለመኗን፣ መማለዷን፣ የሰዎቹን ጭንቅ ለክርስቶስ አቅርባ እንዲቀረፍ መጠየቋን ለምን ጻፈው? ዮሐንስ ይቺን ቃል የጻፈበት ምክንያቱ ምንድን ነች? … የጻፈው ደግሞ

የሚገርማችሁ የሰበከውን ነው፡፡ አንድ ሰው የማያምንበትን አይጽፍም" ብለዋል (1፡07፡20-1፡09፡47 ደቂቃ)፡፡

በዚህ ክፍል ዮሐንስ የጻፈው ስለማን ነው? የሚለውን ለመመለስ ማርያም ለጌታ ያቀረበችውን ሐሳብ ብቻ መምዘዝ ብዙ አያዛልቅም፡፡ ነገር ግን በድርጊቱ መጨረሻ ላይ ዮሐንስ በቃና ዘገሊላው ሰርግ ላይ የተገለጠው የኢየሱስ ክብር እንጂ መምህር ታሪኩ እንዳሉት የማርያም አማላጅነት አይደለም፡፡ "ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ" (ዮሐ. 2÷11)፡፡ የሚለውም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ ጉዳዩ እርስዎ እንዳሉት ቢሆን ኖሮ ‘የማርያምም አማላጅነት ታወቀ’ ብሎ ባከለ ነበር፡፡ ዮሐንስ ግን አላከለም፤ ምክንያቱም (የእርስዎን ቃል ልዋስና) ዮሐንስ የጻፈው የሚያምንበትን ነው፤ ይህ ክፍል ስለማርያም አማላጅነት የሚናገር ቢሆን በጻፈው ነበር፡፡

ሌላው መምህር ታሪኩ የተናገሩት÷ ሐዋርያት ስለማርያም እንዲሁም ስለክርስቶስና ስለጥምቀት ሲያስተምሩ መከራን ተቀበሉ የሚል ነው፡፡ የክርስቶስና የጥምቀት ጉዳይ ይቆየንና÷ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት መከራን የተቀበሉት ስለማርያም አማላጅነት ብፅዕናና ቅድስና ስላስተማሩ ነው በሚለው ላይ እናተኩር፡፡ በመሠረቱ ይህ እንግዳ ትምህርት በዚያ ዘመን አልነበረም፤ በአገራችን ይበልጥ የተስፋፋውም በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ቢሆንም ይህን ትምህርት መቀበልና መስበክ በአገራችን የሚያስከብርና የሚያሸልም÷ ዐውደ ምሕረትም የሚያሰጥ እንጂ ሰደትና መከራ የሚያስከትል አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህን እንግዳ ትምህርት መቃወም ያስድዳል፤ መከራን ያመጣል፡፡ ይኸው እርስዎ በዐውደ ምሕረቱ ላይ እንደልብዎ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ

ያሻዎትን ሲናገሩ ምን መጣብዎ? ተጨበጨበልዎ እንጂ፡፡ ይህን ትምህርት የተቃወሙና ወንጌልን የሰበኩ ግን ከዐውደ ምሕረቱ ተገፍተዋል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት መከራን የተቀበሉት የማርያምን ስም በማንሣታቸው ሳይሆን የኢየሱስን ስም በማንሣታቸው ነው፡፡ በፍርድ አደባባይ የተጠየቁትም በማርያም ስም ለምን ታስተምራላችሁ ተብለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ በማርያም ስም ያስተማሩበት አንድም ጊዜ የለም፡፡ ከኢየሱስ ጋር በተያያዘ ስለማርያም መጥቀስ ማርያምን መስበክ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችልበት አንድም ምክንያት የለም፡፡ ሐዋርያት በአንድ ወቅት ተከሰው የተጠየቁት÷ "በዚህ ስም (በኢየሱስ ስም) እንዳታስተምሩ አጥብቀን አላዘዝናችሁምን?" (የሐዋ. 5÷28) ተብለው ነው፡፡ ተገርፈው ከተለቀቁ በኋላም ደስ ያላቸው ስለ ኢየሱስ ስም የተናቁ ሆነው ስለተቆጠሩ ነው እንጂ ከማርያም ጋር ምንም ግንኙነት የለውም (ቍጥር 41)፡፡ እርስዎ ግን ይህን ገልብጠው ሐዋርያት ያልሰበኩትን ሰብከዋል፤ መከራ ያልተቀበሉበትን ጉዳይ (ስለማርያም መስበክን) መከራ ተቀብለውበታል እያሉ ነውና ዐቋምዎን ቢያስተካክሉ መልካም ነው፡፡

ማርያም የጸጋ መድኀኒት ናት

የአምልኮት መግለጫ የሆኑት ስግደት፣ ምስጋና፣ ውዳሴና የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ሊቀርቡ የሚገባው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ይህ ሰው በቀላሉ ሊገነዘበው የሚችለው የፍጡርነት ግዴታው ነው፡፡ ከክርስትና ውጪ ያሉ ሃይማኖቶችም እንኳ÷ እነዚህን ነገሮች

የሚያቀርቡት አምላካችን ለሚሉት አካል እንጂ ከእርሱ ውጪ ከፋፍለው በተዋረድ አምልኮትን የሚያጋሯቸው ሌሎች ክፍሎች የሉም። በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን የአምልኮት መግለጫ የሆኑት ነገሮች ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን÷ የአምልኮትና የጸጋ በሚል በተዋረድ ለፍጡራንም ይቀርባሉ።

እስከ ዛሬ ማርያምን ጨምሮ ለቅዱሳን መላእክትና ሰዎች ሁሉ የጸጋ ስግደት እንደሚገባቸው ሲሰበክ እንሰማ ነበር። አሁን ደግሞ መምህር ታሪኩ ተሰምቶ የማይታወቅ ማርያም የጸጋ መድኀኒት ናት ሲሉ በስብከታቸው ገልጸዋል። ወደዚህ ያደረሳቸውም በተኣምረ ማርያም÷ ስለማርያም የዓለም መድኀኒትነት የተጻፈው ክፍል ትክክል ነው የሚለው ግትር ዐቋማቸው ነው ማለት ይቻላል ("ተኣምረ ማርያም" ምዕራፍ 12 ቍ. 62 ገጽ 48)።

እርሳቸው የፈለሰፉትን የማርያምን የጸጋ መድኀኒትነት እውነት ለማስመሰል÷ በቀጥታ ስለማርያም መድኀኒትነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ተነሥተው ከመናገር ይልቅ÷ ሌሎች ማነጻጸሪያዎችን መጥቀስንና እዚያው ተኣምረ ማርያም ላይ መርገጥን መርጠዋል፤ ለዚህ ኑፋቄያቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍንጭ እንኳ የላቸውምና።

ለሐሳባቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ለማነጻጸሪያነት የጠቀሱት ሙሴን ለፈርኦን አምላክ አድርጌሃለሁ፤ ሐዋርያትን ደግሞ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ማለቱን ነው። እግዚአብሔር የባሕርይ አምላክ ሲሆን ሙሴን ደግሞ የጸጋ አምላክ አድርጎታል፤ ጌታ ኢየሱስ የባሕርይ ብርሃን ሲሆን ሐዋርያትን የጸጋ ብርሃን አድርጓቸዋልና ማርያም የጸጋ መድኀኒት ብትባል ምንድን ነው ችግሩ? የሚል ማስረጃ አልባና የ"ምናለበት" ክርክር ነው የሚያቀርቡት። ሙሴ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ (ዘፀ. 7÷1) ቢባል በፈርዖን ላይ የበላይ መደረጉን ለማመልከት እንጂ ከእግዚአብሔር በታች

የጸጋ ተብሎ አምላክ ነው ለማለት እንዳልተናገረ ግልጽ ነው፡፡ ሙሴም ብቻ ሳይሆን በእርሱ ዐይነት የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ሲል ጠርቷቸዋል (ዮሐ. 10÷35)፡፡

ሐዋርያትም እንደ ጌታ ብርሃን (ዮሐ. 8÷12) የተባሉበት የባሕርይና የጸጋ በሚል ተዋረድ ወይም ማንም ሊቀርበው ከማይችለው የጌታ ብርሃንነት ጋር ተነጻጽረው ሳይሆን÷ ለጨለማው ዓለም ብርሃን የሆነውን ጌታ በመግለጥ ተግባራቸው ነው፡፡ የጌታ መንገድ ጠራጊ የነበረው መጥምቁ ዮሐንስ ስለብርሃን ሊመሰክር የመጣ እንጂ እርሱ ራሱ ብርሃን አልነበረም (ዮሐ. 1÷6-8)፡፡ ሆኖም ብርሃን ስለሆነው ጌታ ከሰጠው ምስክርነት የተነሣ "እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ፤ እናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ" (ዮሐ. 5÷35) ተብሎ ስለእርሱ ተጽፏል፡፡

መምህር ስለማርያም የጸጋ አዳኝነት÷ ስለሙሴና ስለሐዋርያት በጠቀሱት ዐይነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ የሚሆን አንድ ጥቅስ እንኳ ለምን አልጠቀሱም? የሚል ጥያቄ መሰንዘር ከእሾክ ወይን ይልቀሙ እንደማለት ይሆናልና ይቅር፡፡ ለጸጋ መድኀኒትነቷ በማነጻጸሪያነት የጠቀሱትና "አንድ ተራ ሰው" ያሉት ጎቶንያል ነው፡፡ ጎቶንያል አዳኝ የተባለው በዘመነ መሳፍንት የእስራኤልን ልጆች ከጠላቶቻቸው እጅ ለመታደግ እግዚአብሔር ስላስነሣው ነው፡፡ እንደርሱ ያሉ ብዙ ታዳጊዎችን (አዳኞችን) በዘመነ መሳፍንት እንዳስነሣ በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ተጽፏል፡፡ ዛሬም በዚህ ሁኔታ ከተለያየ ውጫዊ ችግር የሚያድኑ ሰዎችን ጌታ ሊያስነሣ ይችላል፡፡ የነፍስ ድኅነትን ማለትም ከኀጢአትና ከዘላለም ሞት ማዳንን በተመለከተ ግን ከእርሱ በቀር አዳኝ ማንም እንደሌለ መታወቅ አለበት፡፡ ከጠላቶች እጅ የመታደጉን ሥራ ግን

እርስዎ ለማርያም ከሰጡት የጸጋ አዳኝነት ጋር እንዴት ማነጻጸር ይቻላል? ማርያም በጸጋ መድኀኒትነቷስ ማንን ነው ያዳነችው? ከምንስ ነው የምታድነው?

ለመሆኑ የባሕርይ ብለው የፈረጁት የጌታ አዳኝነት ጉድለት ኖሮበት ወይም ፍቱን ሳይሆን ቀርቶ ነው ተጨማሪ መድኀኒት ያስፈለገው? የባሕርይ አዳኝ ያልፈወሰውን በሽታስ የጸጋ አዳኝ እንዴት ይፈውሰዋል ብለው ነው ማርያምን የጸጋ አዳኝ ለማለት የደፈሩት? ሰሙ መምህር! የሚያድነው መድኀኒት የተባለውን ሁሉ መሞከር ሳይሆን ትክክለኛውን መድኀኒት ማግኘት ነው፤ አሊያ "መድኀኒትን ያበዛሽው በከንቱ ነው፤ መዳንም የለሽም" እንደተባለችዋ መሆን ነው (ኤር. 46÷11)።

መምህር ታሪኩ የኢየሱስ አዳኝነት ከጥያቄ ውስጥ እንደማይገባ የተናገሩ ቢሆንም÷ ማርያም የጸጋ አዳኝ ብትባልስ ምንድነው ችግሩ? ሲሉ ይጠይቃሉ። ይህም የኢየሱስ አዳኝነት ብቻውን በቂ አይደለም ብለው የሚያምኑ አስመስሏቸዋል። በኢየሱስ አዳኝነት ያመነ ክርስቲያን ሌላ መድኀኒትን ሊሰብክ አይችልም። ምክንያቱም ቃሉ የባሕርይና የጸጋ ብሎ ሳይከፋፍል "መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" (የሐዋ. 4÷12) ሲል ዘግቶታል፤ አትሞታልም።

በርግጥም ዓለም ሁሉ እንዲድን የተከፈለው ዋጋ አንድ፣ ዋጋውን የከፈለውም አንዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ከክርስቶስ ውጪ በጸጋም ይሁን በሌላ ዓለምን ለማዳን የሚቻለው ሌላ መድኀኒት በዚህ ምድር አልነበረም፤ የለምም። ኖሮ ቢሆን ክርስቶስ ወደዚህ ምድር መምጣትና መከራና ሥቃይ መቀበል ባላስፈለገውም ነበር፤ እንዲያውም

በሥጋ ልደት የምትቀድመውና እርስዎ የጸጋ መድኀኒት ያደረጓት እናቱ ማርያም ባዳነችን ነበር፡፡

መምህር ከተረትነት የማያልፈውን ተኣምረ ማርያምን እውነተኛ ለማድረግ መሞከር የማይቻል በመሆኑ እንደብዙዎቹ ዝምታን ቢመርጡ ይሻል ነበር፡፡ እርስዎ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ የሌለውንና በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያልታወቀውን የተኣምረ ማርያምን ኑፋቄ እውነተኛ ለማድረግ ባደረጉት ጥረት የጌታን አዳኝነት ለመሸራረፍ በመሞከርዎ ትልቅ ኀጢአት ሠርተዋል፡፡ ሕዝቡንም ወደስሕተት መርተዋልና እባክዎ ከልብዎ ንስሓ ይግቡ፡፡

የቤት ሥራ ለመምህር ታሪኩ

መምህር ጥያቄ ከቀረበባቸው የተኣምረ ማርያም ሐሳቦች ለማስተባበል የሞከሩት የተወሰኑትንና ለእርስዎ የተመቹዎትን ብቻ ነው፡፡ አንዳንዶቹን ግን በጊዜ እጥረት ይሁን በመርሳት÷ ወይም ‘ዓሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል’ የሚለውን ብሂል አስታውሰው ምክንያቱ ባይታወቅም ይለፉኝ ብለዋል፡፡ ከጀመሩት አይቀር በ"ቴቄል" ላይ በጥያቄ መልክ ቀርበው ከነበሩትና እንደዋዛ ካለፏቸው ነጥቦች መካከል የሚከተሉት ምላሽ የሚሰጡባቸው የቤት ሥራዎ እንዲሆኑ በድጋሚ ቢቀርቡልዎት፤

1. በተኣምር 12 ቍጥር 52 ላይ "እንደ እኔ ያላችሁ ታጥአን ወንድሞቼ ሆይ እንግዲህስ ወዲህ 16ቱን ሕግጋት ለመፈጸም የእግዚአብሔር ባሮች መሆንን አንሻ፡፡ እሱ በቀትር ጊዜ በመስቀል ላይ እመቤታችሁ እናታችሁ እነሆ እያለ የቃል ኪዳን እመቤት እሷን ሰጥቶናልና፡፡

ስለዚህ ነገር የእመቤታችን የእናታችን የማርያም ባሮች ለመሆን እንሽቀዳደም ብዬ እነግራችኋለሁ" እባክዎ ይህ ምን ማለት ይሆን?

2. በተኣምር 12 ቍጥር 68 ጀምሮ ባለው ክፍል ላይም እንዲሁ 78 ሰዎችን በልቶ ስለነበረው ሰው የተተረከ አለ፡፡ ይህ ሰው እምነት የለሽ ከመሆኑም በላይ÷ ስለእግዚአብሔር ብሎ ለለመነው ሰው ውሃ በመስጠት ፈንታ ተቆጣው፡፡ ስለድንግል ማርያም ብሎ ሲጠይቀው ግን "ይህቺ ደግ እንደሆነች በልመናዋም ከሲኦል የምታድን እንደሆነች እኔም ከሕፃንነቴ ጀምሬ ሰምቼ ነበር" በማለት የለመነውን ውሃ ጥቂት ሰጠው፡፡ እዚህ ላይ ደራሲው እግዚአብሔርን ጨካኝና ሁሉን ወደሲኦል የሚጥል አምላክ አድርጎ ነው ያቀረበው፡፡ በተጨማሪም የእግዚአብሔር ፍርድ በሚዛን የሚለካና በክርክርም ቢሆን እግዚአብሔር በማርያም የሚሸነፍና አስቀድሞ የሰጠውን ብይን የሚቀለብስ ዳኛ ተደርጎ ነው የተሣለው፡፡ ስለዚህስ ምን ይላሉ?

3. በተኣምር 15 እና በተኣምር 39 ቍጥር 1 እስከ መጨረሻ ማርያም ነፍስ ገዳይ ሆና መታያቷን ተአምሩን ያነበቡት ሰዎች ሁሉ የሚናገሩት እውነት ነው፡፡ ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለምናውቃት የጌታ እናት ተስማሚ ጠባይ ነው ይላሉ? ምላሽ ሳይሰጡ ያለፉትስ ለምንድን ነው?

4. ተኣምር 4 ቍ 11 ላይ ጴጥሮስ በማርያም ስም እጆቹ የተቆረጡበትን ሰው ማዳኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በክርስቶስ ስም ካደረገው ጋር እንዴት ይስማማል? የሚለውንስ አልሰሙት ይሆን?

ማጠቃለያ

መምህር ታሪኩ ዛሬ እንደልብዎ የፈነጩባትና ተኣምረ ማርያምን ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ለማሳየት ጥረት ያደረጉባት ይህች ቤተ ክርስቲያን ቀደም ብሎ÷ በኦርቶዶክሳውያን መካከል በተደረገ ሃይማኖታዊ ክርክር አንዱ ተከራካሪ ስለሚያምኑት ነገር ማስረጃ አቅርቡ ቢባሉ ተኣምረ ማርያምን በጠቀሱ ጊዜ "ከአራቱ ጉባኤ አጣህና ስለሃይማኖት ተኣምረ ማርያምን ትጠቅሳለህን" ተብሎ ተነግሮባታል (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከአባ ጎርጎርዮስ ገጽ 84)፡፡ እርስዎ ግን ሃይ ባይ በሌለበት ይህን ለሃይማኖት ምስክርነት የማይጠራ የተረት መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከፍ ብሎ እንዲታይ ለማድረግ ብዙ ደክመዋል፡፡

ያለዐላማ ዕድሉ ስለተገኘ ብቻ መስበክ፣ ሰሚ ስላለ ብቻ ማውራት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል፡፡ ስለዚህ ከመስበክ በፊት ይህን የምሰብከው÷ እንዲህስ የማወራው ለምንድን ነው? ብሎ ማሰብ ተገቢ ነው፡፡

አንዳንድ የዘመናችን ሰባክያን ግን ዐውደ ምሕረቱን ስላገኙት ብቻ ያሻቸውን እየተናገሩበት ይገኛሉ፡፡ የሚያስተምሩበት ርእሰ ጉዳይ ሕዝቡ ወደወንጌል እውነት ዘወር እንዳይልና ባለበት እንዲረግጥ የሚያደርግ መሆኑን ያስተዋሉ አይመስልም፡፡ እንዲህ የሚያደርጉትም የሚሰብኩት ነገር ስሕተት መሆኑ ሳይገባቸው ቀርቶ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን የወንጌሉ ብርሃን ባልበራላቸው ወገኖች ዘንድ ተቀባይነትን ለማትረፍ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ምናልባትም በዚህ ከንቱ ስብከት በጨለማ ያለውን ሕዝብ ዐይን ይበልጥ አሳውሮ የካሴት ገበያውን ለማድራትም ሊሆን ይችላል፡፡

ይሁን እንጂ ጨለማውን ወደድቅድቅ ጨለማነት እየለወጡት መሆኑን ልብ ያሉ አይመስልም፡፡ ለመማር የተሰበሰበው እኮ ክርስቶስ የሞተለት ሕዝብ ነው! ይህ ሕዝብ በእርሳቸው የተሳሳተ ትምህርት ምክንያት ቢጠፋ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚጠየቁበት አልገባቸው ይሆን?

የመምህር ታሪኩ የስብከት ቪሲዲም እንዲህ ዓይነት ነገር የተንጸባረቀበት ነው፡፡ መቼም ጠያቂ የለም ብለው ውሸትን ያለገደብና ያለከልካይ መናገራቸው ሰው የለም ወይ ያሰኛል?

መምህር ጊዜው የተኣምረ ማርያም ሳይሆን የወንጌል ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮም ወንጌሉን መስበክና ሰዎች የነፍሳቸውን መዳን እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ እርስዎ የተከራከሩለትና ለኑፋቄ ትምህርትዎ ዋቢ ያደረጉት ተኣምረ ማርያም በክርስቶስ ፈንታ ፍጡርን የሚሰብክ ፀረ ወንጌል ነው፡፡

ተኣምረ ማርያም ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆነ ትምህርትን የሚያስተምር በመሆኑ ለእርሱ ርእስ ይዞ ትክክል ነው እያሉ መከራከር ራስን ግምት ላይ የሚጥልና የሚያቀልል ተግባር ነው፡፡ መጽሐፉ በቤተ ክርስቲያን በየዕለቱ የሚነበበው ትክክለኛ ስለሆነ አይደለም፡፡ የቆየ ልማድ ነውና ዛሬ ተነሥተን እንዳይነበብ እናድርግ ብንል ያልገባቸው ብዙዎች ሊቃወሙን ይችላሉ በሚል ባለበት የቀጠለ መሆኑ ይታወቃል፡፡ እርስዎ እያደረጉ ያለው ግን ተቃራኒውን ነው፡፡ ይህም ድርጊትዎ የወንጌል ሰባኪ ሳይሆኑ የተኣምረ ማርያም ሰባኪ መሆንዎን አረጋግጧል፡፡

እውን ለሕዝቡ ዛሬ የሚያስፈልገው ለዘመናት ሲያደናቁረን የኖረው ተኣምረ ማርያም ነውን? በፍጹም!! ምናለ ታዲያ ያገኙትን ዕድል የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመታደግ ብቻ ቢጠቀሙበት! ዛሬ ብዙው ሰው

እኮ ከሚገመተው በላይ ፀረ ክርስቶስ በሆነ መንገድ እየነጎደና ክርስትናን እየካደ ነው፡፡ ስለዚህ እርስ በእርስ መነቃቀፉን ትተን በልዩነታችን ዙሪያ ብቻ ብንወያይ÷ እንደገናም ደግሞ ሰው ሊድንበት የሚችልበትን ነገር ብቻ ብናስተምርና የጠፋውን ብንመለስ እግዚአብሔር ይከበራል፡፡ ዛሬ እርስ በርሳችን ስንነቃቀፍ እያመለጠን ያለው ሕዝብ ቀላል አይደለም፤ ይህ ሕዝብ ነገ የጎን ውጋት እንዳይሆንብን ዛሬ ላይ የትኩረት አቅጣጫችንን መቀየር አለብን፡፡ ለሁላችንም ማስተዋሉን ያድለን!!

ዋቢ መጻሕፍት

መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር (2000) ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተታመ፡፡ ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ፡፡

መጽሐፈ ቅዳሴ (ከቀድሞ አባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ንባቡና ትርጓሜው) (1988) አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ሰረቀ ብርሃን ዘወንጌል (መሪጌታ) የዘመናት እንቆቅልሽ ሲፈታ፡፡ ክፍል አንድ፤ ዓለም ማተሚያ ቤት፡፡

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት (1989) ተኣምረ ማርያም፡፡ አዲስ አበባ፡፡

አግዛቸው ተፈራ (ዲያቆን) (መጋቢት 1993) የተቀበረ መክሊት፡፡ ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ፡፡

ዓሥራት ገብረ ማርያም (1983) ትምህርተ መለኮት፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ጌታቸው (መምህር) (1995) ገድል ወይስ ገደል? ሦስተኛ እትም፣ አዲስ አበባ፤ ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ፡፡

ጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር) (1996) ደቂቀ እስጢፋኖስ በሕግ አምላክ ኮሌጅቪል (ሚኒሶታ)፡፡

ጎርጎርዮስ (አባ) (ሰኔ 1974) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ አዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤቱ ያተገለጸ

ጥላሁን መኮንን (1991) መጻሕፍተ ኑፋቄ በመጽሐፍ ቅዱስ ዓይን ሲታዩ፡፡ ክፍል አንድ፤ አፍሪካ ማተሚያ ቤት፡፡

ጽጌ ስጦታው (መምህር) (ግንቦት 1997) ይነጋል፡፡ አዲስ አበባ፤ አፍሪካ ማተሚያ ኃላ. የተ. የግ. ማ፡፡

ቪሲዲዎች

ታሪኩ አበራ (መምህር) (2003) ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ፡፡ ክፍል አንድ፤ ቀኖጥር 4 ቪሲዲ ስብከት፡፡

ኤፍሬም ከተማ (ዘማሪ) (2002) ቴቄል፤ ቪሲዲ ስብከት፡፡